
# በራሂን

## የኢስላም እና የእምነት መሠረቶች

# براهين

## اركان الإسلام والإيمان



አዘጋጅ ሰይፈዲን ሐበሻ 1428 ሂጅራ

# ማውጫ


| ተራ.ቁ | ርዕስ | ገፅ |
|---|---|---|
| 1 | የመፅሐፉ ስያሜ | 3 |
| 2 | አምስቱ የኢስላም መሠረቶች | 5 |
| 3 | የላኢላሃ ኢለላህ ትርጉም | 6 |
| 4 | ሽርክ በሁለት ይከፈላል | 7 |
| 5 | ሰላት | 10 |
| 6 | ዘካት | 13 |
| 7 | የረመዳን ፆም | 14 |
| 8 | ሐጅ | 17 |
| 9 | ስድስቱ የእምነት መሠረቶች | 22 |
| 10 | የውዱእ አደራረግ | 27 |
| 11 | የሰላት አሰጋገድ | 29 |
| 12 | አጫጭር የቁርአን ምዕራፎች | 41 |
| 13 | የሰላት አስፈላጊነት | 44 |
| 14 | ሰላትና ንፅሕና (ጧሃራ) | 45 |
| 15 | በሰላት ወቅት አለባበስ | 46 |
| 16 | የሰላት ወቅቶች | 46 |
| 17 | በሰላት ጊዜ የሚታዩ ስህተቶች | 47 |
| 18 | በሰላት ላይ እያሉ ንግግር ስለመከልከሉ | 48 |
| 19 | ወደ ቀብር ዞሮ መስገድ ስለመከልከሉ | 49 |
| 20 | ሰላት የሚያበላሹ ክስተቶች | 49 |
| 21 | ተውሒድ | 49 |

بسم الله الرحمن الرحيم

**إن الحمد لله نحمده، ونستعينه، ونستغفره، ونعوذ بالله من شرور أنفسنا وسيئات أعمالنا، من يهده الله؛ فلا مضل له، ومن يضلل؛ فلا هادي له. وأشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له، وأشهد أن محمداً عبده ورسوله صلى الله عليه وعلى آله وصحبه وسلم.**

ምስጋና ለአላህ ስለተገባው እናመሰግነዋለን በእርሱም እንረዳለን ምህረትም እንከጅላለን ከነፍሶቻችን ሸሮችና ከወንጀል ሥራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን አላህ ቀጥተኛውን መንገድ የመራው ማንም አያጣመውም የተጣመመን ደግሞ ከአላህ በስተቀር ማንም አይመራውም:: ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባው አምላክ የለም አላህ አንድ ነው ሸርክም የለውም ነብዩ መሐመድም የአላህ አገልጋይ እና መልዕክተኛ መሆናቸውን እንመሰክራለን ሰላምና ሰላት በአላህ መልዕክተኛ በቤተሰባቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን ::

## የመፅሐፉ ስያሜ

ይህ በኢስላም እምነትና መሠረት ዙርያ የተለያዩ መልዕክቶችን አጠር አድርጎ የያዘ መፅሐፍ በራሂን የሚል ስያሜ የተሰጠበት ዋና ምክንያት በመጀመርያ ቡርሃን ማለት ቃሉ የአረብኛ ሲሆን በቁርአን በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተገልፇል ትርጉሙም መረጃ ማለት ነው ለነጠላ ቃል ቡርሃን ከተባለ ለብዙ ቃል በራሂን ይባላል ይህም መረጃዎች ማለት ነው ::

በመሰረቱ የአንድ አላማ ጥሪ ወይንም መልዕክት በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ በቂ መረጃ ማቅረብ ብቸኛው መንገድ ነው ስለዚህ ማንኛውም ወደ ኢስላም የሚጣራ ሙስሊም ወይንም ዳዒ ጥሪ ከሚያደርግላቸው ሰዎች መረጃ (ቡርሃን) ሲጠየቅ ካልተበረዘውና ካልተከለሰው የፈጣሪያችን የአላህ ቃል ቁርአንና ከመልዕክተኛው ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መመርያ ቃል (ሐዲስ) በቂ መረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል:: በተለይ በሃይማኖት ጉዳይ በሚተላለፉ መልዕክቶች መረጃ መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ አላህ በቁርአኑ በተለያየ ቦታ በሚከተለው መልኩ ያቀርበዋል:-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَقَالُوا۟ لَن يَدْخُلَ ٱلْجَنَّةَ إِلَّا مَن كَانَ هُودًا أَوْ نَصَـٰرَىٰ ۗ تِلْكَ أَمَانِيُّهُمْ ۗ قُلْ هَاتُوا۟ بُرْهَـٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَـٰدِقِينَ ﴿١١١﴾ ﴾ البقرة: ١١١

**ትርጉም ((ገነትን ከአይሁድ ወይንም ከክርስቲያን የሆነ ሰው በስተቀር ሌላው አይገባትም አሉ ይህቺ (ከንቱ) ምኞታቸው ናት እውነተኞች እንደሆናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው::))**
አል በቀራህ / **111**

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدْ جَآءَكُم بُرْهَـٰنٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَأَنزَلْنَآ إِلَيْكُمْ نُورًا مُّبِينًا ﴿١٧٤﴾ ﴾ النساء: ١٧٤

**ትርጉም ((እናንት ሰዎች ሆይ ከጌታችሁ ዘንድ በእርግጥ <u>አስረጅ</u> መጣላችሁ ወደናንተም ገላጭ የሆነን ብርሃን (ቁርአንን) አወረድን))**
አል ኒሳእ**174**

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ أَمِ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةً ۖ قُلْ هَاتُوا۟ بُرْهَـٰنَكُمْ ۖ هَـٰذَا ذِكْرُ مَن مَّعِىَ وَذِكْرُ مَن قَبْلِى ۗ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ٱلْحَقَّ ۖ فَهُم مُّعْرِضُونَ ﴿٢٤﴾ ﴾ الأنبياء: ٢٤

**ትርጉም ((ይልቁንም ከርሱ ሌላ አማልክትን ያዙን ? <u>አስረጃችሁን</u> አምጡ ይህ (ቁርአን) እኔ ዘንድ ያለው ሕዝብ መገሰጫ እና ከኔ በፊትም የነበሩ ሕዝቦች መገሰጫ ነው በላቸው በእውነቱ አብዛኞቻቸው እውነቱን አያውቁም ስለዚህ እነሱ እንቢተኞች ናቸው::))** አል አንቢያ / **24**

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَمَن يَدْعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَـٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرْهَـٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلْكَـٰفِرُونَ ﴿١١٧﴾ ﴾ المؤمنون: ١١٧

ትርጉም ((ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ብሎ የሚገዛ በዚህ ላይ ምንም መረጃ የለውም እንዲያውም ምርመራው ጌታው ዘንድ ብቻ ነው እነሆ ከሐዲዎች አይድኑም::)) አል ሙእሚኑን 117

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ أَمَّن يَبْدَؤُاْ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَمَن يَرْزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلْأَرْضِ ۗ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ ۚ قُلْ هَاتُواْ بُرْهَٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٦٤﴾ ﴾ النمل: ٦٤

ትርጉም ((ወይም ያ፣ መፍጠርን የሚጀምር ከዚያም የሚመልሰው ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣቸው አምላክ (ይበልጣልን ? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን ? እውነተኞች እንደሆናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው::)) አል ነምል / 64

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَنَزَعْنَا مِن كُلِّ أُمَّةٍ شَهِيدًا فَقُلْنَا هَاتُواْ بُرْهَٰنَكُمْ فَعَلِمُوٓاْ أَنَّ ٱلْحَقَّ لِلَّهِ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُواْ يَفْتَرُونَ ﴿٧٥﴾ ﴾ القصص: ٧٥

ትርጉም ((ከሕዝቦችም ሁሉ መስካሪን እናወጣለን ማስረጃችሁን አምጡ ስንላቸው (ያን ጊዜ) እውነተኛውም አምላክነት ለአላህ ብቻ መሆኑን ያውቃሉ ይቀጣጥፉት የነበሩትም ከነሱ ይጠፋቸዋል)) አል አል ቀሶስ / 75

ባጠቃላይ ከላይ በተለያዩ የቁርአን አንቀፆች የቀረበው መልዕክት የኢስላም ሃይማኖትን አልቀበልም ብለው ባዕድ አምልኮን ለመረጡ አጋሪዎች ምንም መረጃ እንደሌላቸው አላህ በቁርአኑ አረጋግጧል:: ስለዚህ በኢስላም መልዕክት ውስጥ የሰባት ሰማይና የፍጥረታት ሁሉ አምላክ ከሆነው አላህ የተላከ በጣም ሰፊ የሆነ መረጃዎች (በራሂን) ሰላለ እነሆ የተወሰኑትን መረጃዎች በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተካተው ቀርበዋል::

## አምስቱ የኢስላም መሠረቶች

1ኛ - ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት ጌታ እንደሌለና የነብዩ መሐመድን (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) መልዕክተኛነት በመቀበል (ላኢላሃ ኢለላህ መሐመዱን ረሱሉሏህ) በማለት መመሥከር::
2ኛ - ሰላት መስገድ ::

*3ኛ - ዘካት ማውጣት ::*
*4ኛ - የረመዳንን ወር መፆም ::*
*5ኛ - አቅም እንደፈቀደ በሕይወት ዘመን አንዴ ሐጅ ማድረግ ::*

## 1ኛ . የላኢላሃ ኢለላህ ትርጉም

## شهادة أن لا إله إلا الله هي مفتاح دين الإسلام، وأصله

ላኢላሃ ኢለላህ ብሎ መመስከር ወደ ኢስላም መግቢያ በርና መሠረት ነው ባለፉት ዘመናት የነበሩ ነብያት በጠቅላላ ካነገቡት መልዕክት የመጀመርያው ላኢላሃ ኢለላህ ማለት ሲሆን ይህንኑ መልዕክት ቁርአን ሲያብራራው :-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ﴿٢٥﴾﴾ الأنبياء: ٢٥

**ትርጉም (( ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደ እርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጂ ከመልዕክተኛ አንዱንም አላክንም ))** አል አንቢያ 25

ላኢላሃ ኢለላህ የሚለው ቃል ሁለት ወሳኝ የሆኑ ተቃራኒ መልዕክቶችን ይዟል ይኸውም (ላኢላሃ) ማለት ጌታ የለም የሚል አፍራሽ ቃል ሲሆን (ኢለላህ) ማለት ከአላህ በስተቀር የሚል አፅዳቂ ቃል ነው:: የመጀመራያው (ላኢላሃ) የሚለው አፍራሽ ቃል ትርጉም ከአላህ በስተቀር በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባ መልአክትም ሆነ ነብይ ተራ ሰውም ሆነ ግዑዝ ነገር የለም ማለት ነው ::

(ኢለላህ) የሚለው አፅዳቂ ቃል ትርጉም አላህ በሐቅ ሊያመልኩት የሚገባው ጌታ ነው አምልኮት ማለት ለአንድ ፈጣሪ አምላክ አላህ መንፈስን ማስገዛት ማለት ነው ይኸውም የአላህን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ መቀበል ፣ ከፈጣሪ ከአላህ በስተቀር ከማንኛውም ፍጡር መንፈሳዊ እርዳታ ያለመከጀል ፣ ባጠቃላይ የአምልኮት ዘርፎች ስግደት ፣ መማፀን ፣ ይረዳኛል ብሎ መከጀል ፣ ይጎዳኛል ብሎ መፍራት ፣ ከሕመም ይፈውሰኛል ብሎ ተስፋ ማድረግ ፣ ከደህነት

ከበሽታና ከጭንቀት ያርቀኛል ማለት ፣ ሐብትን ፀጋን ጤናና ድሎት ይለግሰኛል ብሎ መመኘት ለአላህ ብቻ የሚገቡ አምልኮዎች መሆናቸውን ያለአንዳች ጥርጥር ማመን ሲሆን ከላይ የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ እርዳታዎች ፈጣሪ አምላክ አላህን በመተው ከማንኛውም ፍጡር መመኘትና መከጀል ወደ ሽርክ ያመራል ::

## ሽርክ በሁለት ይከፈላል

የመጀመርያው የሽርክ አይነት :- ከአላህ ሌላ አምልኮትን ለፍጡር በማንኛውም መጠን አብዝቶም ሆነ አሳንሶ መስጠት ትልቅ ሽርክ ነው አላህም ሽርክን ፈፅሞ እንደማይምር በቁርአኑ ሲያብራራ:-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغۡفِرُ أَن يُشۡرَكَ بِهِۦ وَيَغۡفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُۚ وَمَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱفۡتَرَىٰٓ إِثۡمًا عَظِيمًا ﴿٤٨﴾ ﴾ النساء: ٤٨

**ይህም ማለት (( አላህ በእሱ የሚያሻርኩትን አይምርም ለፈለገው ግን ሌሎችን ወንጀሎች ይምራል በአላህ ያሻረከ ትልቅን ወንጀል ቀጥፎዋል)).. ኒሳዕ 48**

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَإِذۡ قَالَ لُقۡمَٰنُ لِٱبۡنِهِۦ وَهُوَ يَعِظُهُۥ يَٰبُنَيَّ لَا تُشۡرِكۡ بِٱللَّهِۖ إِنَّ ٱلشِّرۡكَ لَظُلۡمٌ عَظِيمٞ ﴿١٣﴾ ﴾ لقمان: ١٣

**ትርጉሙም (( ሉቅመንም ልጁን ሲገስፀው «እንዲህ» አለው- ልጄ ሆይ ፤በአላህ «ጣዖትን» አታጋራ ማጋራት ትልቅ በደል ነውና ያለውን «አስታውስ»::)) ሉቅማን - 13**

ይህ አንቀፅ የሚያስረዳው በፈጣሪ ላይ ያጋራ ሰው እራሱን እንደበደለ ሰው ነው የሚቆጠረው
ሌላው የቁርአን አንቀፅ:-

-قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ لَقَدْ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْمَسِيحُ ٱبْنُ مَرْيَمَ ۖ وَقَالَ ٱلْمَسِيحُ يَٰبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ ٱعْبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّى وَرَبَّكُمْ ۖ إِنَّهُۥ مَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِ ٱلْجَنَّةَ وَمَأْوَىٰهُ ٱلنَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾ ﴾ المائدة: ٧٢

**ትርጉም ((.. እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ መኖርያውም እሳት ናት ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም ::)) ማዒዳ -72**

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰሐባዎች ከትላልቆቹም ትልቁን ወንጀል ልንገራችሁን ? አሉ ሰሐባዎችም በሉዋ ይንገሩን አሉዋቸው (አንደኛ በአላህ ላይ ማሻረክ እና የእናት አባት ሀቅ ያለመጠበቅ ሁለተኛው ብለው ለጉዳዩ ክብደት ሰጥተውት ከተደገፉበት ቀና ብለው ቁጭ አሉና በሀሰት በማስመስከር ሐቁ ያልሆነውን ሐቂ ነው ማለት ሌላም መጥፎ ቃል መናገር ) በማለት ደጋግመው ሲናገሩ ሰሃባዎቻቸው ምነው ዝም ባሉ ብለው ተመኙ::

ሁለተኛው የሽርክ አይነት የይዩልኝ ኢባዳ ነው:: ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትንሹን ሽርክ ተጠንቀቁት አሉ:: ምንድን ነዉ አሉዋቸዉ? ትንሹ ሽርክ ማለትም ለይዩልኝ ብሎ መስራት ነው ለይዩልኝ ብሎ የሚሰራ ሥራ በአኼራ አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ምንም ምንዳ አይሰጠዉም ለይዩልኝ ብሎ የሚሰራ ሰው በአኼራ እነዚያ በዱንያ ላይ እንዲያዩልኝ ብለህ ያልካቸዉ ሰዎች ምንዳህን ከነሱ ጠይቅ ይባላል::« ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት (የቂያም ቀን ሰዎች በጭፍራ ጭፍራ ሆነዉ ወደ ጀነት በር ይጠጉና የጀነትን ሽታ እያሸተቱ የጀነትን ህንፃ በርቀት እያዩ የጀነት ባለቤትን ቦታ እያዩ ሳሉ አላህ በሉ ወደ ጀሃነም ተመለሱ ለእናንተ እዚህ

በጀነት ምንም ቦታ የላችሁም ይላቸዋል እነሱም ምነዉ ጌታችን መጀመሪያዉኑ የጀነትን ሽታዉንም ሳናሸት ህንፃዉንም ሳናይ እሳት ብትከተን ይሻል ነበር አሁን እንዴት ከጀነት ታርቀናለህ ይሉታል። አላህም «በዱንያ ላይ ስራቹህ ሁሉ ለሰዉ ብላችሁ ነበር አንድም ቀን ልባችሁን ለኔ አልሰጣችሁም ስራችሁ ሁሉ ሰዉ ይይልኝ እገሌ እንዲህ አይነት ሷሊህ ነዉ እንድትባሉ ነዉ ከሰዉ ስትለዩ ለኔ ብላችሁ ለኔ ብቻ የተዋችሁትም ያደረጋችሁትም ነገር የለም እና ቦታችሁ ጀሃነም ነዉ ይባላሉ።) እንዲህም ብለዉ ካሉ በኃላ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አንድ ሰዉ ታዲያ መዳኛዉ ምንድን ነዉ አላቸው «መዳኛዉ አሉት መዳኛዉ ስራችሁን ሁሉ ለሊላህ አድርጉት አላህን አትካዱት ይዩልኝን ተጠንቀቁ ትንሹ አደገኛዉ ሽርክ ነዉና) አሉ።

ከላኢላሃ ኢለላህ የምክርነት ቃል ቀጥሎ የሚተለው መሐመደን ረሱሉላህ የሚለው የምስክርነት ቃል ነው ትርጉሙም ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የአላህ መልዕክተኛ ነብይ መሆናቸውን መመስከር ሲሆን የአላህን አንድነት መስክሮ የነብዩ መሐመድን ነብይነት ያስተባበለ ሙሰሊም ሊባል አይገባውም ።
የነብዩ መሐመድን ነብይነት የመሰከረ ሙስሊም ሁሉ የሚከተለውን መስፈርት ማሟላት አለበት :-

**ومعنى شهادة أن محمدًا رسول الله: الاعتراف برسالته ظاهرًا وباطنًا، وطاعته فيما أمر، وتصديقه فيما أخبر، واجتناب ما نهى عنه وزجر، وألا يعبد الله إلا بما شرع، والاعتراف كذلك بعموم رسالته إلى جميع الثقلين، وأنه خاتم النبيين، لا نبي بعده، إلى أن تقوم الساعة.**

( የነብዩ መሐመድን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነብይነት የመሰከረ ግልፅ በሆነውም ግልፅ ባልሆነውም መልዕክታቸው ማመን ፣ ትዕዛዛቸውን መፈፀም ፣ የተናገሩትን ሁሉ ማመን ፣ የከለከሉትንና

የራቁትን ነገር መከልከል ፣ እሳቸው ባዘዙት መንገድ ብቻ አላህን መገዛት ሲሆን በተጨማሪ የነብዩ መሐመድን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የመጨረሻ ነብይ ስለሆኑ ለሰው ልጆችና ለጋኔሎች (ለጂን ዘሮች) ያመጡትን መልዕክት በጠቅላላ መቀበል ነው ምክንያቱም ከሳቸው በኋላ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ነብይ የለምና ::)

## ሰላት

በኢስላም ሰላት ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰና የኢባዳ ምሰሶ ነው:: ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት ማንኛውም የአላህ ባሪያ መጀመሪያ የውመል ቂያማ የሚታሰበዉ ሰላቱ ነው:: የሰላት አሰጋገዱ ውጤት ተመርምሮ ካለፈ በሁሉም ነገር ያልፋል በሰላት አያያዙ ውጤት ካላለፈ ሌሎቹ ሁሉ ሰደቃው ሐጁ ወላጆቹን መርዳት ባጠቃላይ ኸይር ስራዉ ሁሉ ይበላሸበታል ብለዋል ::

ሰላት መተው ትልቅ ወንጀል ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) «በእኛና በእነሱ በካፊር መካከል ያለዉ ልዩነት ሰላት ነዉ ሰላት የተወ በእርግጥ ከፈረ» ብለዋል::

ሰላት የተው ሰዎች በአኼራ ምን እንደሚጠብቃቸው አላህ በቁርአኑ በሚከተለው መልኩ ያሳውቃል:--

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ مَا سَلَكَكُمْ فِي سَقَرَ ﴿٤٢﴾ قَالُوا لَمْ نَكُ مِنَ الْمُصَلِّينَ ﴿٤٣﴾ وَلَمْ نَكُ نُطْعِمُ الْمِسْكِينَ ﴿٤٤﴾ وَكُنَّا نَخُوضُ مَعَ الْخَائِضِينَ ﴿٤٥﴾ وَكُنَّا نُكَذِّبُ بِيَوْمِ الدِّينِ ﴿٤٦﴾ حَتَّىٰ أَتَانَا الْيَقِينُ ﴿٤٧﴾ ﴾ المدثر: ٤٢ - ٤٧

**የጀሀነም ሰዎችም እንዲህ ይላሉ ትርጉም :-- (( (ይሏቸዋልም) በሰቀር (ጀሐነም) ውስጥ ምን አስገባቹህ? (እነሱም) ይላሉ ከሰጋጆች**

**አልነበርንም ከዘባራቂዎችም ጋር እንዘባርቅ ነበር በፍርዱም ቀን እናስተባብል ነበር እርግጠኛው ሞት እስከመጣብን ድረስ))**

አል ሙደሲር 42-47

ሙስሊሞች አላህን የሚያስታውሱበት ዋነኛዉ መንገድ ሰላት ነው አላህን ከማስታወስ የተዘናጋ በእርግጥ ከሰረ ከቁርአን አንቀፅ መረጃ :--

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُلۡهِكُمۡ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُكُمۡ عَن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ وَمَن يَفۡعَلۡ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٩ ﴾ المنافقون: ٩

**ትርጉም ((እናንት ያመናችሁ ሆይ ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ አያታልላችሁ ይህንንም የሚሰሩ ሰዎች እነዚያ ከሳሪዎቹ ናቸው::)) አል ሙናፊቁን 9**

ከዚህ አንቀፅ አኳያ ሙዕሚን ሆኖ የሚከስር አለ ማለት ነዉ በዱንያ ላይ በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን ግማሹ በስራ ግማሹ በንግድ ሌላዉ በጫወታ በማይረባ ወሬ ሰላትን እንደዋዛ እያሳለፉ የአኼራን ኪሳራ ለመክሰር የተመቻቹ ብዙዎች ናቸው:: ሰዕድ ቢን አቢ ወቃስ ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በቁርአን ላይ ወዮላቸው የተባሉት ሰጋጆች እነማን ናቸው ብሎ ጠየቃቸዉ

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ فَوَيۡلٞ لِّلۡمُصَلِّينَ ٤ ٱلَّذِينَ هُمۡ عَن صَلَاتِهِمۡ سَاهُونَ ٥ ٱلَّذِينَ هُمۡ يُرَآءُونَ ٦ ﴾ الماعون: ٤ - ٦

**ትርጉም ((...ወዮላቸው ለሰጋጆች ፤ ለነዚያ እነሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለሆኑት ፤ (ሰጋጆች) ፤ለነዚያ እነሱ ይዩልኝ ባዮች ለሆኑት..)) አል ማዑን 4 -6**

**ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሲመልሱለት «እነዛ ሰላትን የሚያዘገዩት ናቸዉ አሉት ::**

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት አንድ የአላህ ባሪያ ሰላቱን ወቅቱ እንደገባ ከሰገደ ሰላቱ በብርሀብ ታጅባ ወደ ሰማይ ትወጣና አርሽ ዘንድ እንደደረሰች ለሰጋጁ ወቅቴን እንደጠበቅከኝ አላህ ይጠብቅህ እያለች እስከ የዉመል ቂያማ ዱዓ ታደርግለታለች በተቃራኒዉ ያለወቅቱ የተሰገደች ሰላት ደግሞ በጨለማ ታፍና ወደ ሰማይ እንደደረሰች እንደ ጨርቅ ተጠቅልላ ባለቤቱን ፊቱን እየመታችው እንዳጠፋኸኝ አላህ ያጥፋህ እያለች ትራገማለች »

ሌላዉ ሰላትን አስተካክሎ ስለመስገድ ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሰላት የተሰፈረ ነዉ የሞላ ሞላለት አሉ ሰላትን ያጎደለ ሚዛን እንደሰለበ ወይንም በመስፈሪያ ሲሰፍር እንደሚቀንስ ሰዉ ወይንም በክንድ ሲለካ እንደሚያምታታ ሰዉ ነዉ የሚቆጠረዉ ሰላት ጎደለ (ተቀነሰ) የሚባለዉ በሚሰገድበት ጊዜ ሰባቱን የሰዉነት ክፍሎች መሬት መንካት አለባቸዉ ይኸዉም 1ኛ ግንባርና የአፍንጫዉ ጫፍ 2ኛ እና 3ኛ ሁለት መዳፎች 4ኛ እና 5ኛ ሁለት ጉልበቶች 6ኛ እና 7ኛ የመጫሚያ ደረቶች (የእግር ጫፍ ጣቾችን ጨምሮ) ማለት ሲሆን በሰላት ጊዜ የተዘረዘሩትን የሰዉነት ክፍሎች ሁሉ ካላሳተፈ የጎደለበት የሰወነቱ ክፍል ሰጋጁን ይረግመዋል:: »

በተጨማሪ በሰላት ጊዜ ሙሉ ሀሳቡን ወደ ሰላት አድርጎ በአላህ ፍራቻ የሰገደ ሙሉ ያገኛል ትንሽ ትንሽ ልቡ ወደ ሌላ የሚያስብ ግማሽ የሚያገኝ አለ እሩብና ከዛም በታች የሚያገኝ አለ እንደዉም ሙሉ ለሙሉ ሰላቱን ጀምሮ እስከሚጨርስ ሀሳቡን ወደ ሌላ የሚያደርግ የሰላት አጅር የለዉም አይፃፍለትምም የሚሉ ዓሊሞች አሉ::

ሌላዉ ሰላትን በጀምዓ መስገድ ግዴታ ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት « ለህፃናትና ለሴቶች ባልሰጋ ኖሮ ጀምዓ ሰላት መስጊድ መምጣት ትቶ ቤቱ የተቀመጠን ቤቱን በእሳት እለኩሰዉ ነብር» ብለዋል::

## ዘካት

ዘካት ከአምስቱ የኢስላም መሰረቶች አንዱ ነዉ ዘካ ያለማዉጣት ከዲን እስከማውጣት ያደርሳል:: ለገንዘብ በመሰሰት የአላህን ትእዛዝ ያለመፈፀም ትልቅ ወንጅል ነዉ:: የአላህን ትእዛዝ የሚጥስ ጉዳይ ገጥሞን ጉዳያችንን ካስቀደምን በአላህ አሻረክን ማለት ነዉ በስስት ለሀብት በመስገብገብ ዘካት የከለከለ ሰዉ በቁርአን ስስታምና ሙሽሪክ ተብሎዋል :: መረጃዉም:--

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَلَا يَحْسَبَنَّ ٱلَّذِينَ يَبْخَلُونَ بِمَآ ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضْلِهِۦ هُوَ خَيْرًا لَّهُم ۖ بَلْ هُوَ شَرٌّ لَّهُمْ ۖ سَيُطَوَّقُونَ مَا بَخِلُوا۟ بِهِۦ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ ۗ وَلِلَّهِ مِيرَٰثُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ﴿١٨٠﴾ ﴾ آل عمران: ١٨٠

**ትርጉም ((እነዚያም አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ገንዘብ የሚነፍጉ እርሱ ለነሱ ደግ አይምሰላቸው ይልቁንም እርሱ ለነሱ መጥፎ ነው ያንን በርሱ የነፈጉበትን በትንሳኤ ቀን (እባብ ሆኖ) ይጠለቃሉ የሰማያትና የምድር ውርስ ለአላህ ብቻ ነው አላህም በሚሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው ))** *አል ዒምራን **180***

**ሌላዉ አንቀፅ :-**

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَـٰهُكُمْ إِلَـٰهٌ وَٰحِدٌ فَٱسْتَقِيمُوٓا۟ إِلَيْهِ وَٱسْتَغْفِرُوهُ ۗ وَوَيْلٌ لِّلْمُشْرِكِينَ ﴿٦﴾ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَهُم بِٱلْـَٔاخِرَةِ هُمْ كَـٰفِرُونَ ﴿٧﴾ ﴾ فصلت: ٦ - ٧

**ትርጉም(( (እንግዲህ) በላቸው :- እኔ መሰላችሁ ሰው ብቻ ነኝ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ወደርሱም ቀጥ በሉ ምህረትንም ለምኑት ማለት (ራዕይ) ወደ እኔ ይወርድልኛል**

**ለአጋሪዎች ወዮላቸው «6» ለነዚያ ዘካን ለማይሰጡ እነሱም በመጨረሻይቱ ዓለም እነሱ ከሐዲዎች ለሆኑት (ወዮላቸው)«7» ))**

**ፉሲለት 6-7**

እንግዲህ ዘካን የማይሰጡት ሰዎች በቁርአን በማያሻማ ቃል ሙሽሪክ ተብለዋል ስለዚህ ዘካት ከሰላት በማይተናነስ መልኩ በቁርአን ተደጋግሞ ስለተገለፀ ማንኛውም ሙስሊም አላህ ንብረቱን ያስፋለት ለዘካት የሰላት ያህል ትኩረት መስጠት ግዴታው ነው::

# የረመዳን ፆም

ፆም ማለት ትርጉሙ ከአንድ ነገር መቆጠብ ወይንም መከልከል ማለት ነው ለምሳሌ አላህ በቁርአኑ ስለመርየም ሲያወሳ :-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ فَكُلِي وَٱشْرَبِي وَقَرِّي عَيْنًا فَإِمَّا تَرَيِنَّ مِنَ ٱلْبَشَرِ أَحَدًا فَقُولِيٓ إِنِّي نَذَرْتُ لِلرَّحْمَٰنِ صَوْمًا فَلَنْ أُكَلِّمَ ٱلْيَوْمَ إِنسِيًّا ﴿٢٦﴾ ﴾ مريم: ٢٦

ትርጉሙም **((ብይም ጠጪም ተደሰቺም ከሰዎችም አንድን ብታይ እኔ ለአል ረሕማን ዝምታን (ፆምን) ተስያለሁ ዛሬም ሰውን በፍፁም አላናግርም በይ::))** **መርየም - 26**

እዚህ ላይ (ፆም) የሚለው ቃል የሚያመለክተው የመርየምን ዝም ማለት ወይንም ከንግግር መቆጠብ ማለት ነው::

ሌላው በሽሪዐው ፆም ማለት ከፈጅር ጀምሮ ቀኑን ሙሉ ፀሃይ እስክትጠልቅ ድረስ ከምግብ ከመጠጥና ሌሎች ፆምን ከሚያገድፉ ነገሮች አላህን ለመገዛት ነይቶ መቆጠብ (መታቀብ) ማለት ነው::

## የፆም ደረጃውና ጥቅሙ

**1ኛ -** ፆም ወደ አላህ ከሚቃረቡበት ከትላልቅ የዒባዳ አይነቶች አንዱ ነው :: ሙእሚኖች በፆም ከአላህ የሚያገኙት ምንዳ ወደርና

ልክ የለውም በመፆም ያለፉት ወንጀሎች ይማራሉ፣ በመፆም ፊቶች ከእሳት ይርቃሉ፣ ፆመኞች ልዩ በሆነው የጀነት በር ይገባሉ፣ ፆመኛ ጌታውን ሲገናኝ ይደሰታል::

አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አላህ የአደም ልጆች ሥራቸው ሁሉ ለራሳቸው ነው ፆም ብቻ ሲቀር ፆም የኔ ነው ምንዳውንም የምከፍለው እኔው ነኝ አለ፣ ፆም ጋሻ ነው ከአንዳቹህ መሐል በሚፆምበት ቀን እንዳይረክስ እንዳይጮህ እንዳይሞኝም አንዱ ቢሰድበው ወይንም ቢጣላው እኔ ፆመኛ ነኝ ይበል (ሁለት ጊዜ): የመሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው (በአላህ እምላለሁ) የፆመኛ ሰው የአፉ ጠረን የቂያም ቀን ከምስክ (ሽቶ) ሽታ የተሻለ ይሆናል :ለፆመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት ደስታዎችም ፆመኛ ማታ ሲያፈጥርና በአኼራ ጌታውን ሲገናኝ ነው) ብለዋል:: ቡኻሪ ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት

**2ኛ** - አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የረመዳንን ፆም ግዴታ መሆኑን አውቆ (በኢማን) ምንዳም አገኝበታለሁ ብሎ (በኢሕቲሳብ) የፆመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ሁሉ ይማርለታል) ብለዋል::

ቡኻሪ ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት

**3ኛ** - ሱሄል ቢን ሰዕድ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ጀነት ውስጥ ረያን የሚባል በር አለ የቂያም ቀን ፆሚዎች ብቻ የታሉ ፆሚዎች ተብለው ተጠርተው ከገቡበት በኋላ በሩ ይዘጋል ከነሱ በስተቀር ማንም አይገባበትም) ብለዋል:: ቡኻሪ ሙስሊምና ሌሎችም እንደዘገቡት

ባጠቃላይ ፆም ማለት ሙእሚኖች ፀባያቸውን የሚያንፁበትና የሚያስተካክሉበት ትልቅ ትምህርት ቤት ነው :: ይኸውም ከነፍስ ጋር የሚታገሉበት ፣ ስሜትን ከሸይጣን ጉትጎታ የሚከላከሉበት

፣ሰው የሚጎዳበትን ሃይለኝነቱን ዋጥ አድርጎ ትዕግስት ወደ ተላበሰ ሕይወት የሚመለስበት፣ሥርዐትና ደንብ የሚማርበት ፣ በልቡ ውስጥ እዝነትና ሩህሩህነት የሚፀድቅበት፣ ሙስሊሞች እርስ በእርስ በመተዛዘን የሚተሳሰሩበትና የሚረዳዱበት ፣ ትልቅ ማዕከል ነው ::

## የፆም አይነቶች ሁለት ናቸው

**1ኛ** - ግዴታ (ዋጂብ) የሆነ ፆም:- ግዴታ (ዋጂብ) የሆነው ፆም በሦስት ይከፈላል

ሀ - ወቅቱን ጠብቆ የሚመጣው ግዴታ የሆነው የረመዳን ወር ፆም

ለ - ለጥፋት ማካካሻ የሚፆም (ከፋራ)

ሐ - ሰው በራሱ ላይ የሚጭነው የስለት ፆም (ነዝር) ናቸው::

**2ኛ** - በውዴታ (ተጠውዕ) የሚፆም እንደ ሸዋል ፣ አሹራ ፣ ሰኞና ሃሙስ ፣ የዐረፋ ቀን ፣በየወሩ ሦስት ቀን : የመሳሰሉት ናቸው ::

የረመዳን ፆም ግዴታ የሚሆንባቸው ለአካለ መጠን የደረሱ፣ የአዕምሮም ሆነ የአካል ጤነኞች : ሙስሊም የሆኑና መንገደኛ ያልሆኑ ናቸው ::

የረመዳን ፆም ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች አንዱ ሲሆን ይኸውም በቁርአን በሐዲስና በሕዝበ ሙስሊሙ የተረጋገጠ ነው ::

ስለረመዳን ከቁርአን :-

قَالَ تَعَالَى: ﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى
ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ١٨٣ أَيَّامٗا مَّعۡدُودَٰتٖۚ فَمَن كَانَ مِنكُم
مَّرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۚ وَعَلَى ٱلَّذِينَ يُطِيقُونَهُۥ فِدۡيَةٞ

طَعَامُ مِسْكِينٍ ۖ فَمَن تَطَوَّعَ خَيْرًا فَهُوَ خَيْرٌ لَّهُۥ ۚ وَأَن تَصُومُوا۟ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿١٨٤﴾ البقرة: ١٨٣ - ١٨٤

**ትርጉሙ (( እናንተ ያመናችሁ ሆይ ፆም በነዚያ ከእናንተ በፊት በነበሩ (ህዝቦች) ላይ እንደተደነገገ በእናንተም ላይ ተደነገገ ልትጠነቀቁ ይከጀላል እና የተወሰኑ ቀኖች (ፁሙ) ከናንተ ውስጥ በሺተኛ ወይንም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች የተወሰነውን መፆም አለበት .... ))** አል በቀራ // **183-184** //

አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የረመዳን ወር ሲገባ የሰማይ በሮች ይከፈታሉ የጀሐነም በሮች ይዘጋሉ ሸይጣኖችም ይታሰራሉ» ብለዋል

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

## ሐጅ

ማንኛውም ለአካለ መጠን የደረሰ ሙስሊም አቅሙ እንደፈቀደለት በሕይወት ዘመን አንዴ ሐጅ ማድረግ ግዴታው ነው::

## <u>ሐጅ ግዴታ (ዋጂብ) የሚሆንባቸው</u>

1ኛ - ሙስሊም የሆኑ ::
2ኛ - አዕምሯቸው ጤነኛ የሆኑ ::
3ኛ - ለአካለ መጠን የደረሱ ::
4ኛ - ነፃ የሆኑ አገልጋይ ባርያ ያልሆኑ ::
5ኛ - በገንዘብም ሆነ በጉልበት አቅሙ ያላቸው ::
6ኛ - ለሴቶች አብሯቸው የሚጓዝ የሥጋ ዘመድ (መሕረም) ወይንም ባል ያላቸው :: ናቸው

## <u>ለሴት መሕረም መሆን ያለበት</u>

1ኛ - ሙስሊም የሆነ ::
2ኛ - አዕምሮው ጤነኛ የሆነ ::
3ኛ - ለአካለ መጠን የደረሰና ለሴት የሥጋ ዘመድ ወይንም ባል የሆነ መሆን አለባቸው::

ለሴት የሥጋ ዘመድ (መሕረም) የሚባሉት ልጅ ፣አባት፣ወንድም ፣ አጎት ፣ አያት ፣ የጡት ልጅ ፣ ወንድም ፣ የእንጀራ አባት ናቸው ::

## የሐጅ መሠረቶች (አርካነል ሐጅ) አራት ናቸው

1ኛ - ኢሕራም ማድረግ (ወደ ሐጅ ሥራ ለመግባት መነየት)
2ኛ - ዓረፋ ላይ መቆም
3ኛ - የሐጅ ማጠቃለያ ጠዋፍ (ጠዋፈል ኢፋዳ) ማድረግ
4ኛ - ለሐጅ ሠዕይ ማድረግ :: ናቸው
ከላይ ከተዘረዘሩት ከአራቱ የሐጅ መሠረቶች አንዱ ከጎደለ የጎደለው እስካልተሟላ ድረስ ሐጁ ይበላሻል ::

## የሐጅ ግዴታዎች (ዋጂብ) ሰባት ናቸው

1ኛ - ኢሕራም ከሚቃት ማድረግ ::
2ኛ - ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ የዓረፋ ክልል መቆም ::
3ኛ - ከዓረፋ መልስ ሙዝደሊፋ ማደር ::
4ኛ - አያመ ተሽሪቅ ሦስት ወይንም ሁለት ቀን ዙልሂጃ 11 12 . እና 13 ሚና ማደር
5ኛ - ጀምራት ላይ ጠጠር መወርወር ::
6ኛ - ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር ::
7ኛ - የመሰናበቻ ጠዋፍ ( ጠዋፈል ወዳዕ ) ማድረግ:: ናቸው
ከላይ ከተዘረዘሩት የሐጅ ግዴታዎች አንዱን ያጎደለ ሐጅ (ፊዲያ) አለበት ይኸውም መካ ላይ በግ አርዶ ለድሆች ማከፋፈል ነው::

## ከሐጅ ሱናዎች የተወሰኑት

1ኛ - ኢሕራም ሲደረግ ገላን መታጠብ ::
2ኛ - ለወንዶች ነጭ የኢሕራም ልብስ መልበስ::
3ኛ - ለወንዶች በተልብያ ጊዜ ድምፅን ከፍ ማድረግ ::
4ኛ - ዙልሒጃ ስምንት ( የውመ ተርውያ ) ሚና ማደር ::
5ኛ - ሐጀረል አሥወድን መሳም ::
6ኛ - በጠዋፈል ቁዱም ጊዜ ወንዶች የቀኝ እጅን ግልፅ ማድረግ ::
7ኛ - በጠዋፈል ቁዱም ጊዜ ወንዶች የመጀመርያ ሦስት ዙሮችን መፍጠን:
ከላይ የተዘረዘሩትም ሆነ ሌሎች የሐጅ ሱናዎችን የተወ ሰው ምንም ጥፋትም ሆነ ካሳ የለበትም ::

# የሐጅ ሥነሥርዐት አፈፃፀም በሦስት ይከፈላል

*1ኛ ሙፍሪድ ( ንጥል )*
*2ኛ ቃሪን ( ድርብ )*
*3ኛ ተመቱዕ ( መጠቃቀም ) ናቸው*

## ሦስቱ የሐጅ አፈፃፀም አይነቶች

*ምንም እንኳን የሐጅ አደራረግ ሦስት አይነት ቢሆኑም ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰሐባዎች የመረጡት ተመቱዕ የተባለውን የሐጅ አደራረግ ነው ፡፡ ሦስቱ የሐጅ አደራረግ እንደሚከተለው ይብራራሉ ፡፡*

## ሙፍሪድ

**1ኛ-** *ሙፍሪድ ትርጉሙ ዑምራ ሳይጋራው ሐጅን ለብቻው ማድረግ ማለት ነው፡፡ሐጅን ብቻ ለማድረግ ያሰበ (የነየተ) ሰው የሚከትሉትን የሐጅ አፈፃፀም መከተል አለበት ፤*
*ሀ - ከሚቃት ኢሕራም አድርጎ ለበይክ ሐጅን ብሎ መንቀሳቀስ መካ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሐጅ ለማድረግ ወደ ሚቃት መሄድ የለባቸውም እዛው ባሉበት ቦታ ከቤታቸው ኢሕራም አድርገው ለበይክ ሐጅን በማለት ዙልሒጃ ስምንት ወደ ሚና መንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡*
**ለ** *- የመገቢያ ጠዋፍ (ጠዋፈል ቁዱም) ማድረገ ፡፡ የመገቢያ ጠዋፍ ሳያደርግ ዙልሒጃ ስምንት ወደ ሚና የሄደ ከሚና መልስ የሐጅ መሰረት የሆኑትን ጠዋፈል ኢፋዳ እና ሠዕይን ማድረግ አለበት ፡፡*

## ቃሪን

**2ኛ-** *ቃሪን ማለት ሐጅ እና ዑምራን በአንድ ላይ ማድረግ ማለት ነው በዚህን ጊዜ ሐድይ (ከብት ለመስዋዕት መንዳት) አለበት እንዲህ አይነቱን የሐጅ አፈፃፀም ነብዩ መሀመድ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) ለሰሐቦቻቸው አልመረጡም ለማንኛውም ቃሪን የመረጠ ሰው ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው፡፡*
*ሀ - ከሚቃት ኢሕራም አድርጎ የመስዋዕት ከብት ( ሃድይ ) እየነዳ ለበይክ ዑምራና ሐጅን ብሎ ድምፅን አሰምቶ መነየት፡*
**ለ** *- ጠዋፈል ቁዱም ማድረግ*
**ሐ-** *የሐጅ መሰረት የሆነውን የሰፋና መርዋ ምልልስ ( ሠዕይ ) ማድረግ የፈለገ ከሚና መልስ ማድረግ ይቻላል፡፡*

***መ*** - ከሚና መልስ ጠዋፈል ኢፋዳ ማድረግ

## ተመቱዕ

**3ኛ-** ተመቱዕ ማለት በሐጅ ወራት ውስጥ ሐጅ እና ዑምራ ለማድረግ አስቦ (ሐርሞ) መጀመርያ ዑምራ አድርጎ ሲጨርስ ኢሕራሙን ፈትቶ የሐጅ ወቅት ሲደርስ እንደገና ለሐጅ ኢሕራም ማድረግ አለበት:: የሐጅ ወራት የሚባሉት ሸዋል ዙልቂዳ እና በዙልሒጃ ዘጠኝ ቀኖችና አሥረኛው ሌሊት ናቸው በነዚህ በተጠቀሱት ጊዜያት ዑምራ አድርጎ ሲጨርስ ኢሕራሙን ፈትቶ እስከ ዙልሒጃ ስምንተኛው ቀን ድረስ ቆይቶ ዙልሒጃ ስምንት ካለበት ቦታ ኢሕራም አድርጎ ቀጥታ ወደ ሚና መሄድ አለበት :: ዝርዝሩም እንደሚከተለው ይቀርባል ::

***ሀ*** - ከሚቃት ኢሕራም አድርጎ ( ለበይክ ዑምራ ሙተመቲዓን ኢለል ሐጅ ) ብሎ ድምፅን አሰምቶ መነየት ትርጉሙም (ዑምራ አድርጌ እስከ ሐጅ ድረስ በኢሕራም ወቅት የተከለከሉትን ነገሮች ተጠቅሜ ሐጅ ሲደርስ በድጋሚ ኢሕራም ላደርግ) ማለት ነው በዚህ ምክንያት ማረድ ይገደዳል ማረድ ያልቻለ አሥር ቀን መፆም አለበት አፂፁሙም ሦስት ቀን ሐጅ ላይ ሲሆን ቀሪውን ሰባት ቀን ወደ ሃገሩ ሲመለስ ይፆመዋል ::

***ለ*** - መካ ሐረም ገብቶ ጠዋፈል ቁዱም እና የዑምራን ጠዋፍ ማድረግ ሁለቱንም በአንድ ኒያ ደርቦ ማድረግ ይቻላል ::

***ሐ*** - ለዑምራ ተብሎ የሰፋና መርዋን ኮረብታዎች ሰባት ጊዜ መመላለስ ( ሠዕይ ) ማድረግ::

***መ*** - ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር ለሐጅ ለመላጨት ያሰበ ሰው ማሳጠሩ ይመረጣል ::

***ሠ*** - ኢሕራሙን ፈትቶ ወደ መደበኛ ልብሱ ተመልሶ በኢሕራም ወቅት የተከለከሉ ነገሮች ሁሉ ይፈቀዱለታል በድጋሚ ዙልሒጃ ስምንት ካለበት ቦታ ኢሕራም አድርጎ ወደ ሚና መንቀሳቀስ ::

## <u>የወንዶች አለባበስ በኢሕራም ወቅት</u>

*ሀ* - ወንዶች በኢሕራም ወቅት የሚለብሱት ሁለት ብትን ጨርቆችን አዘጋጅተው አንዱን ከወገብ በታች አገልድመው አንደኛውን ከወገብ በላይ አጣፍተው ሽፍን ያልሆነ ነጠላ ጫማ ይጫማሉ :: በጠዋፈል ቁዱም ወቅት የቀኝ እጅን ከትከሻ ጀምሮ ከኢሕራም ልብስ አሾልኮ ማውጣት ሱና ነው ከዚህ ውጪ ቀኝ እጅን ባገኙበት ቦታ ከኢሕራም ልብስ ማውጣት ስህተት ነው ::

**ለ -** ወንዶች ጭንቅላታቸውን የሚሸፍን ቆብ መድፋት እና ኮፍያ ማድረግ ክልክል ነው ነገር ግን በዣንጥላ ፤በጥላ ሥር እና መኪና ውስጥ፤ መጠለል በአናት ላይ ጊዝ መሸከም የመሳሰሉት አይከለከልም::
**ሐ -** ወንዶች ካፖርት : ሸሚዝ : ሱሪ : ካነቴራ እና የውስጥ ሱሪ የመሳሰሉትን ማንኛውም የተሰፉ በሰውነት የሚጠለቁ ልብሶች መልበስ የለባቸውም : ሽፍን ጫማ መጫማትም ክልክል ነው:: ::
ብትን ጨርቅ እና ነጠላ ጫማ ከጠፋ በተሰፉ ልብሶች እና በሽፍን ጫማ ኢሕራም ማድረግ ይቻላል ::

## የሴቶች አለባበስ በኢሕራም ወቅት

*1ኛ -* ሴቶች በኢሕራም ወቅት ማንኛውንም አይነት ሙሉ ሰውነትን የሚሸፍን ስስ ያልሆነ ሰፊ ልብስ መልበስ አለባቸው :: የእግር ሹራብም ሆነ ሽፍን ጫማ ማድረግም ይፈቀዳል::
*2ኛ -* ሴቶች በኢሕራም ወቅት ፊትን ግጥም አድርጎ የሚሸፍን ጨርቅ (ኒቃብ) ማሰር የለባቸውም እጅንም በጊንት መሸፈን ክልክል ነው::ነገር ግን ኢሕራም ያደረጉ ሴቶች ወንድ መሃል ሲገቡ ፊታቸውን ከአናታቸው በሚወርድ ክንብንብ (ኺማር) መሸፈን አለባቸው :: ሴቶች ሐጅም ላይ ሆነ ከሐጅ ውጪ ፊታቸውንና ሌላ ሰውነታቸውን ለባዕድ ወንድ መግለጥ የለባቸውም ይህ ደግሞ ሸሪዓዊ ግዴታ ነው እንጂ ባህላዊም ሆነ ቤተሰባዊ ልምድ ወይንም መንግስታዊ ጫና አይደለም :: ለዚሁም መረጃ የረሱል (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሐዲስ (ሴት በኢሕራም ወቅት ፊቷን በኒቃብ መሸፈንም ሆነ ጓንት መልበስ የለባትም) ብለዋል ይህ የሚያመለክተው ሴቶች ከሐጅ ውጪ ፊታቸውን በኒቃብ ማሰር እና ጓንት መልበስ እንዳለባቸው ነው :: የረሱል (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) ባለቤት እመት አይሻ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) (በሐጅ ወቅት ፊታችንን ገልፀን ስንጓዝ ባዕድ ወንድ በመጣ ቁጥር እንሸፍን ነበር ) ብለዋል ይህ ደግሞ ሁለተኛው መረጃ ነው ::

## በኢሕራም ወቅት የሚፈቀዱ ነገሮች

***1ኛ*** በኢሕራም ወቅት ፤መነፅር ፤ቀለበት ፤ ሰዐትና ቀበቶ ማድረግ ይቻላል ዣንጥላ መያዝ ቦርሳ ማንገብ የመሳሰሉት ሁሉ ይፈቀዳሉ ::
***2ኛ*** ልብስን መቀየርና ማጠብ ይፈቀዳል በአጋጣሚ ሰውነት ቢቆስል ወይንም ቢደማ ሐጅ ላይ ምንም ችግር አያመጣም ማሸግም ይቻላል፡

በመጨረሻ በኢሕራም ወቅት ቀለል ቀለል ያሉ የተከለከሉ ነገሮችን በመርሳትም ሆነ ባለማወቅ መጠቀም ደም (እርድ) አያስገድድም ።

# ስድስቱ የእምነት መሠረቶች

1. በአላህ ብቸኛ ጌታነት ማመን
2. መላእክት (መላኢካዎች) መኖራቸውን ማመን
3. በየዘመኑ ከአላህ የተላኩ ነብያቶች (መልዕክተኞች) መኖራቸውን ማመን
4. የአላህን መልዕክት የያዙ መፅሐፍት መውረዳቸውን ማመን
5. የዓለም ፍፃሜ የመጨረሻው ቀን እንደሚመጣ ማመን
6. ክስተት ሁሉ በአላህ የተወሰነ (ቀድር) መሆኑን ማመን

## 1ኛ - በአላህ ብቸኛ ጌታነት ማመን

ዕውቀቱ የጠለቀ ጥበቡ የረቀቀ ፍጡራንን ሁሉ የፈጠረ አንድ ሃያል አምላክ መኖሩን ሳይጠራጠሩ በቁርጥ ማመን ። ይህ አምላክ ከማንም ያልተወለደ ማንንም ያልወለደ ፣ እሱን መሳይ ብጤ ፈፅሞ ሊኖረው የማይገባ ፣ ሞት የማይነካው ምንግዜም ነዋሪ ፣ ማንኛውንም ነገር የሚያይ የሚሰማና የሚናገር ፣ የሚሻ እና የሻውን ነገር ሁሉ ከመቅስፈት ማድረግ የሚችል ግልፅና ድብቅ የሆኑ ነገሮችን በጠቅላላ አዋቂ ብቸኛው አምላክ አላህ መሆኑን ማወቅ።

ፈጣሪ አምላካችን አላህ ለመኖሩ ማስረጃው ምንድነው? ቢባል በዚህ ዓለማት ውስጥ የሚታዩት ፍጥረታት በሙሉ ያለአንዳች ፈጣሪ ተገኙ ማለት እንደማንችለው ሁሉ ለምሳሌ ግንብ ተገንብቶ ስናይ ያለግንበኛ ግንቡ በገዛ ራሱ እንዳልቆመ እናምናለን በተጨማሪ ባካባቢያችን የምናያቸው ቁሳቁሶች ለምሳሌ ወንበር ፣ ጠረጴዛ ፣ አልጋ ፣ ሳጥን የመሳሰሉትን ተሰርተው ስናይ እነዚህን መገልገያዎች ለምን እንደሚያገለግሉ መጥኖ የሰራቸው ባለ ሙያ እንዳለ የግዴታ እናምናለን ።
በተመሳሳይ መልኩ ዓለማት ፣ ክዋክብት ፣ ፀሐይ ፣ ጨረቃ መሬት ፣ ሰዎች 'እንስሶች ፣ ዕፀዋትንና የመሳሰሉትን ባጠቃላይ ያለአንዳች ሠሪ ሁሉም እራሳቸውን ፈጠሩ ብለን ማስተባበል እንደማንችለው ሁሉ ፍጥረታትን ሁሉ በፈለገው ቅርፅና መጠን የሰራቸው ዕውቀቱ የጠለቀ ፣ ጥበቡ የረቀቀ ፣

ችሎታው የመጠቀ ፣ ስሙ የላቀ ፣ ብቸኛና ሃያል ፈጣሪ አምላክ ጌታ መኖሩን እናምናለን ::

ይህ ሁሉ ከላይ የተዘረዘሩት ምሳሌዎች አምላካችን አላህ ከሰዎች መካከል እየመረጠ ምንም መልዕክተኛ ባይልክ በማየት ብቻ ፈጣሪ መኖሩን የምንመሰክርባቸው መረጃዎች ናቸው :: ነገር ግን አዛኙ ሩህሩሁ ፈጣሪ አምላካችን አላህ ለሰው ልጆች በማዘን ፈጣሪነቱን በቃሉ በየዘመናቱ በነብያት አማካኝነት አስተዋውቆናል ለአላህ ምስጋና ይገባው::

## 2ኛ - መላእክት (መላኢካዎች) መኖራቸውን ማመን

ረቂቅ የሆኑ የማይታዩና የማይዳሰሱ አላህ ከብርሃን የፈጠራቸው መላእክቶች መኖራቸውን ማመን ከኢስላማዊ የእምነት መሠረቶች አንዱ ነው:: መላእክቶች የአላህን ትእዛዝ በቅንነት የሚፈፅሙ ለፈጠራቸው አላህ ፍፁም ታዛዦች ሲሆኑ አብዛኛው ጊዜ መኖርያቸው በሰማይና ባየር ውስጥ ነው :: ብዛ ቸው ይህን ያህል ነው ብሎ መወሰን አይቻልም ከፈጠራቸው አላህ በስተቀር ትክክለኛ የብዛ ቸውን አሃዝ ማንም አያውቀውም :: ፆታቸው የወንድነትም ሆነ የሴትነት ባሕርይ የላቸውም : የዘወትር ቀለባቸው አላህን ማወደስ ነው : አሥር የዋና ዋናዎቹን ስም እንደሚከተለው ይጠቀሳሉ :-

1) ጂብሪል 2) ሚካኢል 3) ኢስራፊል 4) መለከል መውት 5) ረቂብ 6) ዓቲድ 7) ሙንከር 8) ነኪር 9) ረድዋን 10) ማሊክ :: ናቸው እነኚህ ሥማቸው የተጠቀሱትም ሆነ ሌሎች ከአላህ የተሰጣቸው ልዩ ልዩ የስራ መደብ አላቸው::

## 3ኛ - በነብያቶች ወይንም በመልዕክተኞች ማመን

በየዘመኑ ከአላህ የተላኩ ነብያቶች ወይንም መልዕክተኞች መኖራቸውን ማመን በኢስላም ከኢማን መሠረቶች አንዱ ነው:: ነብያቶች ማለት አላህ በየዘመናቱ ከሰው ልጆች ዘር መርጦ ለፍጡራኑ የሰው ልጆች መልዕክት እንዲያስተላልፉ እንዲያስተምሩና ወደ መልካም ጎዳና እንዲመሩ የመረጣቸው አገልጋዮቹ ናቸው ::

በየዘመናቱ የሰው ልጆችን ትክለኛውን የአምልኮ መንገድ ለማስያዝ ከፈጣሪ አላህ የተላኩ ነብያት መኖራቸውን ቁርአን በሰፊው ስለሚያስረዳ ማመን የእያንዳንዱ ሙስሊም ግዴታ ነው ::

የብዛ ቸውን ቁጥር በትክክል ባይታወቅም በብዙዎች የሙስሊም ምሁራን ዘንድ አንድ መቶ ሃያ አራት ሺ ናቸው ይባላል ::

ነብያቶች ከኀጥያት የራቁ ፣ እውነተኞች ታማኞች ብልሆች መልክታቸውን በትጋት አድራሾችና ፣ በሚደርስባቸው ፈተና ታጋሾች ናቸው:: ከላይ ከተጠቀሰው የአሃዛቸው ብዛት ውስጥ ሦስት መቶ አሥራ ሦስቱ መልእክተኛ (ሩሱል) ሲባሉ ከነዚህም ውስጥ ሃያ አምስቱ ስማቸው በቁርአን ተዘርዝሯል:: የነዚህን ነብያት ሥም ማወቁ ተገቢ ስለሆነ እነሆ የስም ዝርዝራቸው ቀርቧል :-

## በቁርአን ሥማቸውና ታሪካቸው የተወሱ ነቢያቶቸ ሥም

1. አደም
2. ኢድሪስ
3. ኑሕ
4. ሁድ
5. ሷሊህ
6. ኢብራሂም
7. ሉጥ
8. ኢስማዒል
9. ኢስሐቅ
10. የዕቁብ
11. ዩሱፍ
12. አዩብ
13. ሹዐይብ
14. ሃሩን
15. ሙሳ
16. አልየስዕ
17. ዙልኪፍል
18. ዳውድ
19. ሱለይማን
20. ኢልያስ
21. ዩኑስ
22. ዘከርያ
23. ያህያ
24. ኢሳ (ኢየሱስ)
25. መሓመድ ናቸው (በሁሉም የአላህ ሰላምና ሰላት ይውረድ

ከላይ ከተዘረዘሩት ሃያ አምስት መልእክተኞች አምስቱ በደረጃ ከሁሉም የበለጡ ሲሆኑ በቁርአን መከራን ቻይና ታጋሽ (ኡሉልያዝም) በመባል ይታወቃሉ እነሱም :-

1. ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)
2. ነብዩ ኢብራሂም (ዓለይሂ ሰላም)
3. ነብዩ ሙሳ (ዓለይሂ ሰላም)
4. ነብዩ ኢሳ (ዓለይሂ ሰላም)
5. ነብዩ ኑሕ (ዐለይሂ ሰላም) ናቸው

ባጠቃላይ የመጀመርያው ነብይ :- ነብዩ አደም (አለይሂ ሰላም) ሲሆኑ የመጨረሻው ነብይ ፣ ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ናቸው::

## 4ኛ - ከሰማይ ከአላህ በተላኩ መፅሐፍት ማመን

የአላህን መልዕክት የያዙ መተለያዩ ዘመናት በተወሰኑ ነቢያት አማካኝነት ወደ ሕዝቦች የተላኩ መፅሐፍት መውረዳቸውን ማመን በኢስላም ከኢማን መሠረቶች አንዱ ነው:: ከሰማይ ከአላህ ዘንድ መፅሐፍ የወረደላቸው ወይንም የተሰጡት ዋና ዋናዎቹ አራቱ የሚከተሉት ናቸው :-

1. ተውራት ለነብዩ ሙሳ የወረደ
2. ዘቡር ለነብዩ ዳውድ የወረደ
3. ኢንጂል ለነብዩ ኢሳ (ኢየሱስ) የተሰጠ
4. ቁርአን (ፉርቃን) ለነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የወረደ ነው ::

ሌሎችም ፁሁፎች የተሰጣቸው ነብያቶች ሲኖሩ ማንኛውም ሰው በሚኖርበት ዘመን ወይን አካባቢ ለተላከው ነብይ ተከታይ መሆን ግዴታ አለበት  አሁን ባለንበት የመጨረሻው ነብይ ዘመን ያለን ሰዎች በጠቅላላ በየትኛውም ሐገር የሚገኝ የአዳም ዘር የመጨረሻውን መልዕክተኛ ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ተከታይ መሆን ግዴታው ነው :: በመጨረሻው ነብይ ዘመን የሚኖር ማንኛውም የሰው ዘር የቀድሞዎቹ ነብያት ተከታይ ነኝ ብሎ ፈጣሪ አምላክ አላህን እገዛለሁ አመልካለሁ ቢል ፈጣሪ አላህ ዘንድ አምልኮው ተቀባይነት የለውም:: እንኳንስ ተራው ሕዝብ አይደለም በአሁኑ ዘመን ከቀድሞዎቹ ነብያት ለምሳሌ ነብዩ ሙሳ ወይንም ነብዩ ኢሳ (ኢየሱስ) ቢኖሩ የነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ተከታይ እንዲሆኑ ይገደዱ ነበር :: እንዲያውም ነብዩ ኢየሱስ በመጨረሻው ትንሳኤ (ቂያማ) መቃረቢያ ዘመን ካሉበት ከሰማይ ወርደው የኢስላም ተከታይ ሆነው የሞታሉ :: ይህ ሁሉ ከላይ የተዘረዘሩት መልዕክት ከቁርአንና ከሐዲስ በቂ መረጃ አላቸው::

## 5ኛ - የዓለም ፍፃሜ (የመጨረሻው ቀን) እንደሚመጣ ማመን


ይህ የምንኖርበት ዓለም የመጨረሻ ትንሳኤ (የውመል ቂያማ) የሚባል የምድረ - ዓለም ፍፃሜ የሆነ ቀን እንደሚመጣ ማመን ከኢስላም የእምነት መሰረቶች አንዱ ነው ::
በሰማይና በምድር ያለው ፍጡር በጠቅላላ ጠፍቶ አላህ ብቻውን የሚቀርበት ቀን ይመጣል:: በመቀጠልም እኛ ሰዎች በድጋሚ ነፍስና አካላችን ተገጣጥሞ ተቀስቅሰን ፈጣሪ አምላካችን አላህ ዘንድ ቀርበን ቀደም ሲል ምድር ላይ እያለን በሠራነው ሥራ ለጥብቅ ምርመራ ቀርበን ጥሩም ሆነ መጥፎ እንደየስራችን የስራችንን ዋጋ ይገጥመናል::
በመጪው ዓለም ሥራው ሲመዘን ኀጢአቱ የበዛበት በገሃነም የተወሰነ ጊዜ ተቀጥቶ በፈጣሪ አምላክ አላህ የማያጋራ ከሆነ ወደ ገነት የመመለስ ዕድል ሊገጥመው ይችላል:: በአላህ የሚያጋራ ከሆነና አምልኮን ከአላህ አሳልፎ ለፍጡር የሚሰጥ ከሆነ መጨረሻ ለሌለው ገሃነም ይዳረጋል ::
በተጨማሪ በአላህ አንድነት ብቻ እያመነ በትላልቆቹም ሆነ በትናንሾቹ የአምልኮት ዘርፎች ምንም ሳያሻርክ አላህን ብቻ የሚያመልክ ከሆነና ከተለያዩ ወንጀሎች ለምሳሌ እንደ ሃሜት ፣ ዝሙት ፣ ነፍስ ማጥፋት ፣ ስርቆሽ ፣ አራጣ መብላትና ማብላት ፣ ከመሳሰሉትና ከሌሎችም ወንጀሎች የጠራ ሰው ያለአንዳች የገሃንም ቅጣት በፈጣሪ አላህ እዝነት ሞት ህመም ችግር የሌለበት የዘላለም ደስታና ተድላ ወዳለበት ወደ ገነት በቀጥታ የመግባት እድል ሊገጥመው ይችላል : አላህ ከእንደዚህ አይነቶቹ ያድርገን:: ባጠቃላይ የመጨረሻው ቀን ማለት ለሰው ልጆች እንደየሥራቸው ፍርድ የሚሰጥበት ቀን ነው::

## 6ኛ - በቀድር (በውሳኔ) ማመን

በምድርም ሆነ በሰማይ በሰዎች ፣ በመልአክትም ሆነ በሌሎች ፍጡራን ባለፉት ዘመናት የተከሰተው ድርጊት ፣ አሁን እየተከሰተ ያለው ድርጊትና ወደፊት የሚከሰተው ድርጊት ሁሉ በአላህ ተወስኖ ያለፈ መሆኑን ማመን በኢስላም ከኢማን መሰረቶች አንዱ ነው ::
ማንኛውም ነገር ከመሆኑ በፊት ከጥንቱ አላህ ዘንድ የመሆኛ ው ጊዜ ተወስኖና ተለክቶ ተፅፎ ተቀምጧል በዛው በተወሰነበት ጊዜ በአላህ ፈቃድ ይሆናል እንጂ ከተወሰነበት ጊዜ በፊት ቀድሞ ወይንም ዘግይቶ የሚሆን ነገር የለም::


ማንኛውም በፍጥረታት ዙርያ የሚከሰቱ መልካምም ሆነ መጠፎ ነገር የሚወሰነው በአላህ ነው በእርግጥ የአላህ ውሳኔ ለፈተና ይሁን ለምንዳ ፣ ለቅጣት ይሁን ለቁጣ ምክንያቱን የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው:: ሙስሊም ውሳኔዎች በጠቅላላ (ቀዷና ቀድር) በአላህ ተወስኖ ያለፈ ጉዳይ መሆኑን ማመን ግዴታው ነው::

## የውዱእ አደራረግና  የሰላት አሰጋገድ




1ኛ - ውዱእ ለማድረግ በልብ መነየትና ቢስሚላህ ብሎ መጀመር በውዱእ ወቅት ውሃን መቆጠብ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ረሱል (ሰለላሁዓለይሂ ወሰለም) በእፍኛቸው ነበር ውዱእ የሚያደርጉት







2ኛ- መጀመርያ የእጅን መዳፎች ማጠብ ከእንቅልፍ የተነሱ ከሆነ ማጠቡ ግዴታ ይሆናል::
ከውዱእ በፊት ጥርስን መፋቅ ሱና ነው::
በቀኝ እጅ እፍኝ ውሃ ይዞ ወደ አፍ በማስገባት አፍን በደንብ መጉመጥመጥ:
በዚሁ እፍኝ የተረፈውን ውሃ ወደ አፍንጫ ውስጥ ስቦ በማስገባት በግራ እጅ ተናፍጦ ማውጣት ፃመኛ ካልሆኑ ውሃውን ወደ አፍንጫ በደንብ ስቦ ማስገባት::

3ኛ - ፊትን በሙሉ ማጠብ ይኸውም ወደ ጎን ከቀኝ ጆሮ እስከ ግራ ጆሮ በቁመት ከራስ ፀጉርመብቀያ ጀምሮ ወደ ታች ጉንጭን ወይንም




የፂም መጨረሻ ድረስ ማጠብ::በቁጥር 3 ፎቶ ላይ እንደሚታየው ፂምን በመዳፍ እያሻሹ ወይንም በጣት ዘርዘር አድርጎ ማጠብ:

4ኛ ሁለት እጆችን ከጣቶች ጫፍ ጀምሮ እስከ ክንድ መታጠፍያ ድረስ ማጠብ:: ትጥበቱ የሚጀመረው ከቀኝ እጅ ሲሆን በጣቶች መካከል መታሸት አለበት::

ማስታወሻ :- ሁለት እጆችን ማጠብ ማለት መዳፍና ጣቶችን ጨምሮ እስከ ክንድ መታጠፍያ ድረስ ነው::

5ኛ የራስ ፀጉርን ውሃ በራሰ እጅ ከፊት የራስ ፀጉር ጀምሮ ወደ ኋላ የራስ ፀጉር መጨረሻ ድረስ በማበስ በድጋሚ ወደፊት አብሶ በዛው ውሃ በራስ አመልካች ጣትን ወደ ጆሮ ውስጥ በማስገባት ማሸትና የጆሮን የውጭ ክፍል በአውራ ጣት ማሸት::

6ኛ ሁለት እግሮችን ከቁርጭምጭሚት ጀምሮ የእግር ጣቶችን ጨምሮ ማጠብ ::
በትጥበት ጊዜ ከቀኝ እግር በመጀመርና በየጣቶች መሐል ማጠብ ያስፈልጋል ::

በዚህ መልኩ የውዱእ አደራረግ ተጠናቀቀ ማለት ነው

# የሰላት አሰጋገድ

አንድ ሙስሊም ሰላት ለመስገድ ሲፈልግ የግዴታ ጦሃራ መሆንና ለሰላት ሲቆም ፊቱን ወደ ቂብላህ አዙሮ አላሁ አክበር ማለት አለበት ምክንያቱም ወደ ሰላት ለመግባት ውዱእ ማድረግ ፣ ወደ ቂብላህ መዞርና አላሁ አክበር ማለት መሠረታዊ ግዴታዎች ናቸው ::

ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሀዲሳቸው

، لقوله صلى الله عليه وسلم : ( إذا قمت إلى الصلاة فأسبغ الوضوء ، ثم استقبل القبلة فكبر )

ትርጉም:-

(ለሰላት ስትቆሙ ውዱእ አሟልታችሁ ወደ ቂብላ ተቅጣጩና አላሁ አክበር በሉ::) ብለዋል

-- አላሁ አክበር ሲባል የግድ ከአንደበት ቃል መውጣት አለበት ድምፅን ከፍ ማድረግ ግን ግዴታ አይደለም ::

-- ዲዳ (መናገር የሚሳነው ሰው) ከሆነ ተክቢራን በልቡ በኒያ ማለት አለበት::



ስዕል ቁጥር 1

-- (በቁ 1 ስዕል) ላይእንደሚታየው በተክቢራ ግዜ ሁለት እጆችን ወደ ትከሻ ድረስ ከፍ ማድረግ ሱና ነው የእጅ ጣቶችም ዘርዘር ማለት የለባቸውም ኢብኑ ዑመር እንዳወሩት

( أن النبي صلى الله عليه وسلم كان يرفع يديه حذو منكبيه إذا افتتح الصلاة ، وإذا كبر للركوع ، وإذا رفع رأسه من الركوع )

ትርጉም:-

(ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሰላት ሲጀምሩ ፣ ጉልበታቸውን ይዘው ጎንበስ ለማለት (ሩኩዕ ለማድረግ) ሲሉ ፣ እና ከሩኩዕ ሲነሱ እጆቻቸውን ወደ ትከሻቸው ከፍ ያደርጉ ነበር::) ብለዋል



ሌላው በቁጥር 2 ስዕል ላይ እንደሚታየው ማሊክ ቢን አል ሑዌሪስ እንዳወሩት

**( أن رسول الله صلى الله عليه وسلم كان إذا كبر رفع يديه حتى يحاذي بهما أذنيه ]**

(ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ተክቢራ በሚሉበት ግዜ ሁለት እጆቻቸውን ወደ ጆሮቻቸው ያስጠጉት ነበር ፡፡) ብለዋል

ስዕል ቁጥር 2




ስዕል ቁጥር 3

በመቀጠልም በቁጥር 3 ስዕል ላይ እንደሚታየው (ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ተክቢራ ካሉ በኋላ የግራ እጃቸውን መገጣጠሚያ በቀኝ እጃቸው ጨብጠው ይዘው ደረታቸው ላይ ያሳርፉታል




ስዕል ቁጥር 4

ወይንም በቁጥር 4 ስዕል ላይ እንደሚታየው ቀኝ እጃቸውን በግራ እጃቸው መዳፍ ጀርባና ክንድ ላይ አሳርፈው ደረታቸውን ይይዛሉ ፡፡

ዋኢል ቢን ሐጅር ባወሩት ሐዲስ (ነብዩ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ሰላት ሲቆሙ የቀኝ እጃቸውን በግራ እጃቸው መዳፍ ጀርባና ክንዳቸው ላይ ያሳርፉ ነበር አይናቸውንም በሱጁድ ወቅት ግንባራቸው የሚያርፍበት ቦታ ላይ ብቻ ይመለከቱ ነበር ብለዋል፡፡

ዓኢሻ (ረዲየላሁ አንሃ) ባወሩት ሐዲስ (ረሱል ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሰላት ሲቆሙ አይናቸውን በሱጁድ ጊዜ ግንባራቸው ከሚያርፍበት ቦታ አይነቅሉም ነበር ብለዋል፡፡

በመቀጠልም የሰላት መክፈቻ ዱዓ ያደርጋሉ ይኸውም (ሱብሐነከ አላሁመ ወቢሐምዲከ ወተባረከ ኢስሙከ ወተዓላ ጀዱከ ወላ ኢላሃ ገይሩክ) ይሉ ነበር
ትርጉም :- (ከጉድለት የጠራህ አላህ ሆይ ምስጋና ተገባህ ስምህ ብሩክ ስጦታህም የላቀ ነው ካንተ በስተቀር አምላክ የለም )

ወይንም (አላሁመ ባዒድ በይኒ ወበይኒ ኸጣያዩ ከማ በዓድተ በይነል መሽሪቅ ወል መግሪብ አላሁመ ነቂኒ ሚን ኸጣያዩ ከማ ዩነቂ ተውበል አብየድ ሚነደነስ አላሁመ እግስልኒ ቢል ማአ ወተልጅ ወልበረድ) ይሉ ነበር

ትርጉም:- (አላህ ሆይ ምሥራቅና ምዕራብን እንዳራራቅከው እኔና ወንጀሌንም አራርቅ)

በመቀጠል በአላህ ለመጠበቅ (አዑዙ ቢላህ ሚነሽይጣኒረጂም) ይላል ትርጉም (ከሽይጣን ክፋት በአላህ እጠበቃለሁ) ማለት ነው

ከዛም (ቢሰሚላህ አረሕማን አረሂም) ይላል
ትርጉም (በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩሕሩሕ በጣም አዛኝ በሆነው ::) ማለት ነው
በማስከተል ከቁርአን ሱረቱል ፋቲሐህ ይቀራል ምክንያቱም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)

*( لا صلاة لمن لم يقرأ بفاتحة الكتاب ) :*

( የቁርአን መክፈቻ (ፋቲሐን) ያልቀራ ሰላት የለውም ብለዋል) ምክንያቱም የሰላት መሠረት ስለሆነ ያለፋቲሐ ሰላቱ ትክክል አይሆንም (እንዳጋጣሚ አዲስ ሰለምቴ ሆኖ ፋቲሐ መቅራት የማይችል ከሆነ እስኪለምድ ድረስ ማናኛውንም አይነት ዚክር ማለት ይችላል::)

## ሱረቱል ፋቲሐ (የመክፈቻይቱ ምዕራፍ)

﴿ بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ١ ﴾ الفاتحة: ١

**(1) ቢስሚላህ አረሕማን አረሒም፣**
**-- በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩሕሩሕ በጣም አዛኝ በሆነው ::**

﴿ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢ ﴾ الفاتحة: ٢

**(2) አልሐምዱ ሊላህ ረቢል ዓለሚን፣**

**-- ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለሆነው::**

﴿ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ۝٣ ﴾ الفاتحة: ٣

**(3) አረሕማኒ ረሒም፣**
**-- እጅግ በጣም ሩሕሩሕ በጣም አዛኝ**

﴿ مَٰلِكِ يَوۡمِ ٱلدِّينِ ۝٤ ﴾ الفاتحة: ٤

**(4) መሊኪ የውሚዲን፣**
**የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው::**

﴿ إِيَّاكَ نَعۡبُدُ وَإِيَّاكَ نَسۡتَعِينُ ۝٥ ﴾ الفاتحة: ٥

**(5) ኢያከ ነዕቡዱ ወኢያከ ነስተዒን፣**
**-- አንተን ብቻ እንገዛለን አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን::**

﴿ ٱهۡدِنَا ٱلصِّرَٰطَ ٱلۡمُسۡتَقِيمَ ۝٦ ﴾ الفاتحة: ٦

**(6) እህዲነ ሲራጠል ሙስተቂም፣**
**-- ቀጥተኛውን መንገድ ምራን::**

﴿ صِرَٰطَ ٱلَّذِينَ أَنۡعَمۡتَ عَلَيۡهِمۡ غَيۡرِ ٱلۡمَغۡضُوبِ عَلَيۡهِمۡ وَلَا ٱلضَّآلِّينَ ۝٧ ﴾ الفاتحة: ٧

**(7) ሲራጠለዚነ አንዓምተ ዓለይሂም ገይሪል መግዱቢ ዓለይሂም ወለዷሊን፣**
**-- የነዚያን በነርሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ)::**

ሰጋጁ ፋቲሐ መቅራት የማይችል ከሆነ የገራለትን የቁርአን አንቀፅ መቅራት ይችላል: ከቁርአን አንቀፅ ምንም ማንበብ የማይችል ከሆነ ::


(ሱብሐን አላህ ወልሐምዱ ሊላህ ወላኢላሃ ኢለላህ ወላሁ አክበር ወላ ሐውለ ወላ ቀወተ ኢላ ቢላህ) ማለት ይችላል ነገር ግን ለሰላት የሚሆኑ አጫጭር የቁርአን ምዕራፎችን በፍጥነት መማር አለበት::

የፋቲሐ ምዕራፍ ከቀሩ በኋላ የገራለትን አጭር የቁርአን ምዕራፍ ሙሉውን ወይንም የተወሰነውን መቅራት አለበት::


በመቀጠል አላሁ አክበር በማለት እጆቹን መጀመርያ ሰላት ሲጀምር እንዳነሳ ወደ ትከሻው ወይንም ወደ ጆሮዎቹ ከፍ አድርጎ አላሁ አክበር በማለት ሩኩዕ ማድረግ :: ሩኩዕ ማለት በሁለት እጆች

ጣቶችን ዘርዘር አድርጎ ሁለት ጉልበትን ይዞ በጣም ሳያዘቀዝቁ በጥቂቱም ሳያጎብጡ በመካከለኛ ወገብን ለጥ አድርጎ ጎንበስ ማለት ነው:: (መይበልጥ ለመረዳት ቁጥር 5 ና 6 ስዕልን ይመልከቱ)
በሩኩዕ ወቅት ሱብሐነ ረቢየል ዓዚም) አንድ ግዜ ማለት ግዴታ ሲሆን ከአንድ በላይ ሱና ነው::

-- በሩኩዕ ወቅት = ሱብሐነከ አላሁመ ረበና ወቢሐምዲከ አላሁመ እግፍርሊ= ወይንም = ሱቡሑን ቁዱስ ረቡል መላኢከተ ወሩሕ ማለት የተወደደ ዱዓ ነው::



ስዕል ቁጥር 5 ና 6



ወገቡ ቀጥ ስላላለ ስህተት የሆነ የሩኩዕ አደራረግ



በጣም ስለተጎነበሱ ስህተት የሆነ የሩኩዕ አደራረግ

በመቀጠል (ሰሚዓላሁ ሊመን ሐሚዳ) በማለት እራስን ከፍ ማድረግ በዚህ ወቅት በቁጥር 1 እና 2 ስዕል ላይ እንደሚታየው እጆችን ከፍ ማድረግ ሱና ነው::
ከሩኩዕ ተነስቶ ቀጥ ብለው ከቆሙ በኋላ



ሰሚዓላሁ ሊመን ሐሚዳ ሲባል አሚን እንደሚል ሰው እጆችን መዘርጋት ስህተት ነው



ስዕል ቁጥር 7 ጂም



ስዕል ቁጥር 8 ዳል

= ረበና ለከል ሐምድ = ወይንም
= ረበና ወለከል ሐምድ = ወይንም
= አላሁመ ረበና ለከል ሐምድ = ወይንም
= አላሁመ ረበና ወለከል ሐምድ = ከአራቱ አንዱን መርጦ ማለት
ሌላ ተጨማሪ ዱዓ የፈለገ

= ሚልአ ሰማዋቲ ወልአርድ ወሚልአ ማሺእት ሚን ሸይኢ በዕድ አህለ ሰናእ ወልመጅድ አሐቁ ማቃለል ዓብድ ወኩለና ለከ ዓብድ ላማኒዕ ሊማ አዕጠይት ወላሙዕጢ ሊማ መነዕት ወላየንፋዕ ዛል ጀድ ሚንከል ጀድ = ማለት ይችላል

-- ከሩኩዕ ከተነሱ በኋላ ረበና ለከል ሐምድ ሲባልም ሆነ ሌሎች ዱዓዎች ሲደረግ (በቁጥር 3 እና 4 ስዕል) ላይ እንደሚታየው በቀኝ እጅ የግራ እጅን መዳፍ ጀርባ ይዞ ደረት ላይ ማሳረፍ ሱና ነው።

በመቀጠል አላሁ አክበር በማለት ሱጁድ ማለት
በተራ ቁጥር 7 ላይ እንደሚታየው ሱጁድ ሲወረድ ከተቻለ ከእጅ በፊት አስቀድሞ በጉልበት መውረድ ሱና ነው ።
ዋኢል ቢን ሀጅር ባወራው ሐዲስ ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሱጁድ ሲያደርጉ ከእጃቸው በፊት ጉልበታቸውን ያስቀድሙ ነበር።
ማንኛውም ሰጋጅ በሱጁድ ወቅት ሰባት የሰውነት ክፍሎችን ማለትም ሁለት እግሮችን ፣ ሁለት ጉልበቶችን ፣ ሁለት እጆችንና ግንባርን ከአፍንጫ ጋር መሬት ማስነካት አለበት። በሱጁድ ወቅት ከላይ ከተዘረዘሩት የሰውነት ክፍሎች አንዱንም ቢሆን መሬት ያለማስነካት ክልክል ነው።

-- (በቁጥር 7 ጂም ስዕል ላይ) እንደሚታየው ሰጋጅ በሕመም ምክንያት በደንብ ሱጁድ ማለት የማይችል ከሆነ



ስዕል ቁጥር 9



ስዕል ቁጥር 10



ስዕል ቁጥር 11

በሚችለው መጠን ወደ ሱጁድ መቃረብ አለበት::

-- በሱጁድ ወቅት (በቁጥር 7 ዳል) እንደሚታየው አጠገብ ያለን ሰው የማያስቸግሩ ከሆነ ክንድን ከወገብ ጎን ማራቅ ሱና ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሱጁድ ሲያደርጉ ብብታቸው እስኪታይ ድረስ ክንዳቸውን ያሰፉት ነበር::
- በሱጁድ ወቅት ሆድን ከታፋ ማራቅ ሱና ነው::
በተጨማሪ በሱጁድ ወቅት ሁለት ጉልበቶችን በመጠኑ ማራራቅና ከበስተኋላ ሁለት ተረከዞችን መግጠም ሱና ነው::

(በቁጥር 9 ስዕል) ላይ Xንደሚታየው በሱጁድ ወቅት ክንዶችን መሬት ላይ መዘርጋት የተጠላ ነው : ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ማናችሁም ብትሆኑ ክንዳችሁን እንደ ውሻ አትዘርጉት ብለዋል:: ነገር ግን (በቁጥር 10 ስዕል) ላይ እንደሚታየው ሰጋጅ ሱጁድ ሲያስረዝም ከደከመው በሁለት ክንዶች የእግር ታፋን መደገፍ ይቻላል::
-- በሱጁድ ወቅት አንድ ግዜ (ሱብሃነ ረቢየል አዕላ) ማለት ግዴታ ነው ከአንድ ግዜ በላይ ሱና ነው::
በሱጁድ ወቅት (ሱቡሑን ቁዱስ ረቡል መላኢካ ወሩሕ) ወይንም (ሱብሐነከ አላሁመ ረበና ወቢሐምዲከ አላሁመ አግፍርሊ) ማለት ይወደዳል ::

-- በመቀጠል ከሱጁድ (አላሁ አክበር በማለት ቁጭ ይላል አቀማመጡ (በቁጥር 11 ስዕል) ላይ እንደሚታየው የቀኝ እግርን ጣቶች መሬት ላይ በመትከል ተረከዝን ወደላይ አቁሞ በግራ እግር መጫሚያ ላይ መቀመጥ ::
በዚህን ግዜ ሁለተኛውን ሱጁድ ከማድረግ በፊት (ረቢ አግፍርሊ ወርሐምኒ ወአህዲኒ




የተሳሳተ አቀማመጥ




ስዕል ቁጥር 12




ስዕል ቁጥር 13

**ወዓፍኒ ወርዙቅኒ ) ማለት ይወደደዳል:: (በቁጥር 12 እና 13 ስዕል) ላይ እንደሚታየው በሱጁድ መካከል ሲቀመጡ የቀኝ እጅን ወደ ጉልበት አስጠግቶ የቀኝ እግር ጭን ላይ ማስቀመጥ የግራ እጅንም ወደ ጉልበት አስጠግቶ በግራ ጭን ላይ ማስቀመጥ::**

**-- በመቀጠል ልክ የመጀመሪያ ሱጁድእንዳደረጉት ሁለተኛውን ሱጁድ ማድረግ**


**-- በመቀጠል ሁለተኛውን ረከዓ ለመጀመር (አላሁ አክበር) በማለት በሁለት እጆች በመመርኮዝ ሁለት ጉልበቶችን ብድግ አድርጎ ቀና ብሎ መቆም::**

**-- በመቀጠል ሁለተኛውን ረከዓት የመክፈቻ ዱዓና (አዑዙ ቢላህ ሚነሸይጣኒረጂም) ማለት ሲቀር ልክ አንደኛውን ረከዓት እንደሰገደ አድርጎ ይሰግዳል --**

**በመቀጠል (በቁጥር 11 ስዕል) ላይ እንደሚታየው ሁለተኛውን ረከዓት ከጨረሱ በኋላ የመጀመርያውን ተሸሁድ ለማለት በግራ እግር መጫሚያ ላይ መቀመጥ እጁንም (በቁጥር 14 ስዕል) ላይ እንደሚታየው ሸሃዳና ዱኣ ሲያደርግ የቀኝ እጅ ጣቶችን በጠቅላላ ጨብጦ የአመላካች ጣትን ብቻ ማመላከት (በቁጥር 15 ስዕል) ላይ እንደሚታየው የግራ እጅን ጣቶች ዘርግቶ ጭን ላይ በማስቀመጥ እንደሚከተለው አታሕየት ይላል :-**

**: ( التحيات لله والصلوات والطيبات ، السلام عليك أيها النبي ورحمة الله وبركاته ، السلام علينا وعلى عباد الله الصالحين أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمداً عبده ورسوله . )**

**-- (አተሕያቱ ሊላሂ ወሰለዋቱ ወጠያባቱ ፤ አሰላሙ አለይከ አዩሃነብዩ ወራሕመቱላሂ**




ወበረካቱሁ ፣ አሰላሙ አለይና ወዓላ ዒባደላሂ አሷሊሂና ፣ አሽሃዱ አን ላኢላሃ ኢለላህ ወአሽሃዱ አነ መሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ::)

ትርጉም:- ክብር ሰላቶችና መልካም ነገሮች ለአላህ ነው ፣ አንቱ ነብይ ሆይ የአላህ እዝነቱና በረከቱ ለርስዎ ይሁን ፣ ሰላም ለእኛና ለመልካሞቹ የአላህ ባሮች ይሁን ፣ ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚገዙት ሌላ አምላክ እንደሌለና መሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ::ማለት



ስዕል ቁጥር 16

-- ሰላቱ ባለሦሥት ወይንም ባለአራት ረከዓት ማለትም ዙሁር ፣ አሥር ፣ በግሪብ ወይንም ኢሻ ሆኖ ሁለተኛው ተሸሁድ ላይ አቀማመጡ ከአንደኛው ተሸሁድ አቀማመጥ ይለያል ይኸውም (በቁጥር 16 ስዕል) ላይ እንደሚታየው የግራ እግርን አሾልኮ በቀኝ እግር ሥር ማድረግና በተጨማሪ የቀኝ እግርን ጣቶች መሬት ላይ ሰክቶ ተረከዝን ወደ ላይ በማቆም መቀመጫን መሬት አስነክቶ ተደላድሎ በመቀመጥ ልክ እንደመጀመርያው ተሸሁድ አተሕያት እስከመጨረሻ ማለትና በተጨማሪ ሰለዋት ማለት ይኸውም:-



ስዕል ቁጥር 17

***( اللهم صلِّ على محمد وعلى آل محمد ، كما صليت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد ، وبارك على محمد وعلى آل محمد كما باركت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد . )***

-- (አላሁመሰለ ዓላ መሐመድ ወዓላ ዓሊ መሐመድ  ከማ ሰለይተ ዓላ ኢብራሒመ ወዓለ ኢብራሂመ ኢነከ ሐሚዱን መጂድ ፣ ወባሪክ ዓላ መሐመድ ወዓላ ዓለ መሐመድ ከማ ባረክተ ዓላ ኢብራሂመ ወዓላ አለ ኢብራሂመ ኢነከ ሐሚዱን መጂድ )

ትርጉም፡- (አላህ ሆይ በመሐመድና በቤተሰባቸው ላይ ሰላምህን አውርድ ልክ በኢብራሂምና በቤተሰባቸው ላይ እንዳወረድክ አንተ ምስጉንና ሃያል ነህና ፣ በመሐመድና በቤተሰባቸው ላይ በረከትህን አውርድ ልክ በኢብራሂምና በቤተሰባቸው ላይ በረከትህን እንዳወረድክ አንተ ምስጉንና ሃያል ነህና።)
በተጨማሪ የሚከተሉትን ዱዓ ማለት ይወደዳል፡-

***( اللهم إني أعوذ بك من عذاب جهنم ، وعذاب القبر ، ومن فتنة المحيا والممات ، ومن فتنة    المسيح الدجال***

አላሁመ ኢኒ አዑዝ ቢከ ሚን አዛብ ጀሀነም ፣ ወዓዛበል ቀብር ፣ ወሚን ፊትነቲል መሕያ ወል መማት ፣ ወሚን ፊትነቲል መሲሒል ደጃል ።
ትጉም፡- (አላህ ሆይ ፣ ከጀሀነም ስቃይ ፣ ከቀብር ውስጥ ቅጣት ፣ በሕይወትም ሆነ ከሞት በኋላ ከመፈተን ፣ በመሲሒል ደጃል ከመፈተን በአንተ እጠበቃለሁ።)

ሌላው ዱዓ

**( اللهم أعني على ذكرك وشكرك وحسن عبادتك )**

(አላሁመ አዒኒ ዓላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስን ዒባደቲክ)
ትርጉም፡- አላህ ሆይ አንተን እንዳስታውስህና እንዳመሰግንህ እርዳኝ።

ከፈለጉም ሌላ ዱዓ መጨመር ይቻላል፡

በመቀጠል (አሰላም ዓለይኩም ወራሕመቱላሂ ) በማለት መጀመርያ ወደ ቀኝ ቀጥሎ ወደ ግራ በማሰላመት የሰላቱ መጨረሻ ይሆናል።

አሰላምተው ሰላት ካጠናቀቁ በኋላ በማስረጃ የተረጋገጡትን አዝካሮች ማለት ሱና ነው ከነሱም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል

( استغفر الله ، أستغفر الله ، أستغفر الله ، اللهم أنت السلام ومنك السلام تباركت ياذا الجلال والإكرام .

አስተግፍረሏህ ፣ አስተግፍረሏህ ፣ አስተግፍረሏህ ፣ አላሁመ አንተ ሰላም ወሚንከ ሰላም ተባረክተ ያዘል ጀላል ወል ኢክራም::

ትርጉም :- አላህን ምህረት እጠይቃለሁ : (ሦሥት ጊዜ) አላህ ሆይ አንተ ሰላም ነህ ሰላምም አንተ ዘንድ ነው ፣ የእልቅናና የቸርነት ባለቤት (አላህ) ሆይ ብሩክ ነህ::

ሌላው ዱዓ:-

: ( لا إله إلا الله وحده لا شريك له ، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير ، اللهم لا مانع لما أعطيت ولا معطي لما منعت ولا ينفع ذا الـجَد منك الـجَد

(ላኢላሃ ኢለላህ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወህወ ዓላ ኩሉ ሸይኢ ቀዲር ፣ አላሁመ ላ ማኒዕ ሊማ አዕጠይት ወላ ሙዕጢ ሊማ መነዕት ወላ የንፋዕ ዚል ጀድ ሚንከል ጀድ::)

ትርጉም:- ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት አምላክ የለም (አላህ በጌትነቱ) ብቸኛና ተጋሪ የለውም ፣ ንግሥናና ምስጋና ለርሱ ብቻ ነው እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ (ሃያል) ነው ፣ አላህ ሆይ አንተ ለሰጠኸው ማንም ሚከለክለው የለም አንተ ለከለከልከው ደግሞ ማንም ሰጪ የለውም ፣ ባለሐብትም ምንም አይጠቅምም ሐብት ማለት አንተ ዘንድ ነው ::

ሌላው ዱዓ

- ( لا إله إلا الله وحده لا شريك له ، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير ، لا إله إلا الله ولا نعبد إلا إياه ، له النعمة وله الفضل وله الثناء الحسن ، لا إله الله مخلصين له الدين ولو كره الكافرون )

-- ላኢላሃ ኢለላህ ወሕደሁ ላሸሪከለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወህወ ዓላ ኩሊ ሸይኢ ቀዲር
ላኢላሃ ኢለላህ ወላነዕቡዱ ኢላ ኢያሁ ለሁ ኒዕመቱ ወለሁል ፈድል ወለሁል ሰናኡል ሐሰን ፣ ላኢላሃ ኢለላህ ሙኽሊሲነ ለሁዲን ወለው ከሪሃል ካፊሩን)

ትርጉም:- ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት ጌታ የለም (አላህ በጌትነቱ) ብቸኛና ተጋሪ የለውም ፣ ንግሥናና ምስጋና ለርሱ ብቻ ነው እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ (ሃያል) ነው ፣
-- ከአላህ በስተቀር በሃቅ የሚገዙት ጌታ የለም ከሱ በስተቀር ማንንም አንገዛም ፀጋ በረከትና ያማረ ውዳሴ ለሱ ብቻ ነው ፣
-- ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት ጌታ የለም ምንም እንኳን ከሃዲያን ቢጠሉም ሃይማኖት ፍፁም የሱ ብቻ ነው::

በመቀጠል ከሰላት በኋላ የሚከተሉት አዝካሮች ይባላሉ:-

**ثم يقول : ( سبحان الله. والحمد لله. والله أكبر ) (33) مرة ، ويقول بعدها مرة واحدة ) لا إله إلا الله وحده لا شريك له ، له الملك وله الحمد ، وهو على كل شيء قدير**

(ሱብሃነላህ ፣ ወልሐምዱ ሊላህ ፣ ወላሁአክበር) 33 ጊዜ በማለት አንድ ጊዜ-- (ላኢላሃ ኢለላህ ወሕደሁ ላሸሪከለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወህወ ዓላ ኩሊ ሽይኢ ቀዲር )ይባላል

ትርጉም-- ( አላህ ከጉድለት የጠራ ነው ፣ ምስጋናም ለአላህ ነው ፣ አላህም የላቀ ነው:: 33 ጊዜ ይባላልና በመጨረሻ አንድ ግዜ ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚገዙት ጌታ የለም (አላህ በጌትነቱ) ብቸኛና ተጋሪ የለውም ፣ ንግሥናና ምስጋና ለርሱ ብቻ ነው እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ (ሃያል) ነው ፣ ) ይላል::

በማስከተል ከቁርአን ፣ አያተል ኩርሲ ፣ ቁል ሁወላሁ አሃድ ፣ ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ ፣ እና ቁልአዑዙ ቢረቢናስ ፣ መቅራት ሱና ነው የቁርአን አንቀፆቹም:-

## አጫጭር የቁርአን ምዕራፎች

## አያቱል ኩርሲ ፣ ሱረቱል በቀራ (የላም ምዕራፍ)

﴿ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُۚ لَا تَأۡخُذُهُۥ سِنَةٞ وَلَا نَوۡمٞۚ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيۡءٖ مِّنۡ عِلۡمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَۚ وَسِعَ كُرۡسِيُّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفۡظُهُمَاۚ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ٢٥٥ ﴾ البقرة: ٢٥٥

**(አላሁ ላ ኢላሃ ኢላ ሁወል ሐዩል ቀዩም ላተእኹዙሁ ሲነቱ ወላ ነውሙ ለሁ ማፊሰማዋቲ ወማ ፊልአርድ መንዘለዚ የሽፊዑ ዒንደሁ ኢላ ቢኢዝኒሂ የዕለሙ ማ በይነ አይዲሂም ወማ ኽልፊሁም ወላ ዩሒጡነ ቢሸይኢን ሚን ዒልሚሂ ኢላ ቢማሻአ ወሲዓ ኩርሲዩሁ ሰማዋቲ ወልአርድ ወላ የኡዱሁ ሒፍዙሁማ ወሁወል ዓሊዩል ዓዚም) -- አል በቀራህ - 255**

**ትርጉም:-**
**አላህ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም ሕያው እራሱን ቻይ ነው ማንገላጃትም ሆነ እንቅልፍ አትይዘውም በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው ያ እርሱ ዘንድ በፍቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡራን) ከፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም) መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ ጥበቃቸውንም አያቅተውም እርሱም የሁሉም በላይ ታላቅ ነው::**

## ሱረቱል ኢኽላስ (የፍፁምነት : ምዕራፍ)

﴿ قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۝١ ﴾ الإخلاص: ١

**ቁል ሁወ አላሁ አሃድ ፤**
**በል እርሱ አላህ አንድ ነው::**

﴿ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۝٢ ﴾ الإخلاص: ٢

**አላሁ ሰመድ ፤**
**አላህ (የሁሉም) መጠጊያ ነው::**

﴿ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ۝٣ ﴾ الإخلاص: ٣

**ለም የሊድ ወለም ዩለድ ፤**
**አልወለደም አልተወለደምም**

﴿ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ۝٤ ﴾ الإخلاص: ٤

**ወለም የኩን ለሁ ኩፉወን አሃድ ፤**
**ለርሱም አንድም ብጤ የለውም::**

## ሱረቱል ፈለቅ ፣ (የተፈልቃቂው ምዕራፍ)

﴿ قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلۡفَلَقِ ١ ﴾ الفلق: ١

**ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ ፣**
**በል - በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ::**

﴿ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ٢ ﴾ الفلق: ٢

**ሚን ሸሪ ማኽለቅ ፣**
**ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ክፋት::**

﴿ وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ٣ ﴾ الفلق: ٣

**ወሚን ሸሪ ጋሲቂን ኢዛ ወቀብ ፣**
**ከሌሊትም ክፋት ባጨለመ ጊዜ::**

﴿ وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِي ٱلۡعُقَدِ ٤ ﴾ الفلق: ٤

**ወሚን ሸሪ ነፋሣቲ ፊል ዑቀድ**
**በተቋጠሩ (ክሮች) ላይ ተፊዎች ከሆኑት (ደጋሚ) ሴቶችም ክፋት::**

﴿ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ٥ ﴾ الفلق: ٥

**ወሚን ሸሪ ሐሲዲን ኢዛ ሐሰድ ፣**
**ከምቀኛም ክፋት በተመቀኘ ጊዜ:: (እጠበቃለሁ በል::)**

## ሱረቱል ናስ (የሰዎች ምዕራፍ)

﴿ قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ١ ﴾ الناس: ١

**ቁል አዑዙ ቢረቢናስ፣**
**በል - በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ**

﴿ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ٢ ﴾ الناس: ٢

**መሊኪናስ**
**የሰዎች ሁሉ ንጉስ በሆነው**

﴿ إِلَٰهِ ٱلنَّاسِ ٣ ﴾ الناس: ٣

**ኢላሂናስ፣**
**የሰዎች አምላክ በሆነው::**

﴿ مِن شَرِّ ٱلۡوَسۡوَاسِ ٱلۡخَنَّاسِ ﴿٤﴾ ﴾ الناس: ٤

**ሚን ሸሪል ወስዋሲል ኸናስ ፣**
**ብቅ እልም ባይ ከሆነው ጎትጓች (ሰይጣን) ክፋት፡፡**

﴿ ٱلَّذِي يُوَسۡوِسُ فِي صُدُورِ ٱلنَّاسِ ﴿٥﴾ ﴾ الناس: ٥

**አለዚ ዩወስዊሱ ፊሱዱሪ ናስ፣**
**ከዛ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከሆነው፡፡**

﴿ مِنَ ٱلۡجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ﴿٦﴾ ﴾ الناس: ٦

**ሚነል ጂነቲ ወናስ፣**
**ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል)፡፡**

**--** ሙስሊም ሰላቶችን በጠቅላላ ሳይዘናጋ እየተጠባበቀ መስጊድ በመሄድ በጀምዓ መስገድ ይገባዋል በአላህ ፈቃድም ከሚድኑት ሰዎች እንዲሆን ይከጀላልና፡፡

## የሰላት አስፈላጊነት

**1 -** የሰላት ዋና አስፈላጊነት አላህን ለማተለቅና ለመገዛት የሚያገለግል ሲሆን ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠ ነው ፡፡ ሰላት የተደነገገው ሌሎች የኢስላም መሠረቶች እንደተገነቡት ሳይሆን ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ቀጥታ ወደ ሰማይ በመውጣት ከአላህ ዘንድ አምስቱን ሰላቶች ተቀብለዋል ፡፡ በተረፈ በሰላት ዙርያ ያሉትን ሌሎች ብያኔዎች (አሕካም) ምድር ከወረዱ በኋላ በጅብሪል አማካኝነት ነው የተቀበሉት ፡፡

ሰላት በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያለች ሴት ስትቀር ለአቅም አዳም በደረሱ አዕምሯቸው ጤነኛ በሆኑ ወንድና ሴት ሙስሊሞች ላይ ግዴታ ሆኖዋል፡፡

ሰላት በተለይ ለወንዶች በሕብረት (በጀምዓ) መስጊድ መስገድ የበለጠ ምንዳ የሚያስገኝ ሲሆን በጉዞም ላይ ሆነ ሳይጓዙ በቀንም ሆነ በሌሊት ፈፅሞ የማይተው የግዴታ ዒባዳ ነው፡፡

ሰላት የመስገጃው ወቅቱ ፣ አይነቱና ብዛቱ በሰፊው ተብራርቶዋል ስለዚህ ሰላት ከሌሎች ዒባዳዎች በቀደምትነት የሚታይ ነው፡፡

ሰላት ዘወትር አላህንና ሙስሊም ባርያውን የሚያገናኝ ብቸኛ መስመር ነው፡፡

ሰላት ሙስሊሞችን በቀን አምስት ጊዜ አቅርቦ የሚያገናኝ ሲሆን የዓመት በዓል (ዒዶች) ሳይቀሩ የሚከበሩትና ሚደምቁት በሰላት ነው::

-- ሰላት ሙስሊምን ከአላህ ጋር የሚያገናኝና የሚያቀራርብ ሲሆን ቋንቋውም በተዋበው የአላህ ቃል በቁርአን የታጀበ ነው::

## ሰላትና ንፅሕና (ጧሃራ)

-- አላህ በቁርአኑ

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا قُمۡتُمۡ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغۡسِلُواْ وُجُوهَكُمۡ وَأَيۡدِيَكُمۡ إِلَى ٱلۡمَرَافِقِ وَٱمۡسَحُواْ بِرُءُوسِكُمۡ وَأَرۡجُلَكُمۡ إِلَى ٱلۡكَعۡبَيۡنِۚ وَإِن كُنتُمۡ جُنُبٗا فَٱطَّهَّرُواْۚ وَإِن كُنتُم مَّرۡضَىٰٓ أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٍ أَوۡ جَآءَ أَحَدٞ مِّنكُم مِّنَ ٱلۡغَآئِطِ أَوۡ لَٰمَسۡتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَلَمۡ تَجِدُواْ مَآءٗ فَتَيَمَّمُواْ صَعِيدٗا طَيِّبٗا فَٱمۡسَحُواْ بِوُجُوهِكُمۡ وَأَيۡدِيكُم مِّنۡهُۚ مَا يُرِيدُ ٱللَّهُ لِيَجۡعَلَ عَلَيۡكُم مِّنۡ حَرَجٖ وَلَٰكِن يُرِيدُ لِيُطَهِّرَكُمۡ وَلِيُتِمَّ نِعۡمَتَهُۥ عَلَيۡكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ٦﴾ المائدة: ٦

**ትርጉም (( እናንት ያመናችሁ ሆይ ወደ ሰላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ ፣ ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ) የረከሳችሁም ብትሆኑ (ገላችሁን) ታጠቡ ሕመምተኞች ወይንም በጉዞ ላይ ብትሆኑ ወይንም ከናንተ አንዳችሁ ከዓይነ ምድር ቢመጣው ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና (ብትገናኙ) ውሃን ባታገኙ ንፁህን የምድር ገፅ (በማበስ) አስቡ ከሱም ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁን አብሱ አላህ በናንተ ላይ ምንም ችግር ሊያደርግ አይሻም :: ግን ታመሰግኑ ዘንድ ሊጠራችሁና ፀጋውን በናንተ ላይ ሊሞላ ይሻል ::))** አል ማኢዳ 6

-- ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ አንሁ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁዓለይሂ ወሰለም (አላህ ሰላትን ያለጧሃራ (ያለንፅሕና) አይቀበልም) ብለዋል::

-- ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ረዲየሏሁ አንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (የሰላት መክፈቻው ጧሃራ ፣ መግቢያው ተክቢራ ሲሆን ማጠቃለያው ተስሊም ነው) ብለዋል፡፡

አቡ ዳውድ ዘግቦት አልባኒ ትክክል ብለውታል

## በሰላት ወቅት አለባበስ

-- የሙእሚኖች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ አንሃ) ባወሩት ሐዲስ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ለአካለ መጠን የደረሰች ሴት ሰላቲ ያለክንብንብ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

-- አቢ ሁረይራ (ረዲየሏሁ አንሁ) ባወሩት ሐዲስ አንድ ሰው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (አንዳችሁ አንድ ጨርቅ ብቻ ካለው ወደ ትከሻው ሳያደርስ አይስገድ) ብለዋል፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት

## የሰላት ወቅቶች

-- ቡረይዳ (ረዲየሏሁ አንሁ) ባወሩት ሐዲስ አንድ ሰው ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ስለሰላት ወቅት ጠየቃቸው እሳቸውም ከኛ ጋር ሁለት ቀን ስገድ አሉትና፡፡ ፀሐይ ከአናት በላይ ዘንበል እንዳለች ቢላል (ረዲየሏሁ አንሁ) አዛን እንዲል አዘዙት (ከጥቂት ቆይታ በኋላ) በድጋሚ ኢቃም እንዲል አዘው የዙሁር ሰላትን አሰገዱ ፣ ከዛም ፀሐይ ከፍ ብላ ንፁህ ነጭ ስትመስል የአስርን ሰላት አሰገዱ ፣ በመቀጠል ፀሐይ እንደጠለቀች የመግሪብ ሰላትን አሰገዱ ፡፡ በመቀጠል ጀንበር (አድማስ) በጠቅላላ ጠፍቶ ጨለማ ሲሆን ዒሻን አሰገዱ፡፡ በመቀጠል (በማግስቱ) ውጋገን ሲሆን የፈጅር ሰላት አሰገዱ፡፡

በሁለተኛው ቀን ፀሃይ በረድ ስትል የዙሁር ሰላትን አሰገዱ በመቀጠል በመጀመርያ ቀን አስር ባሰገዱበት ወቅት ፀሃይ ደርሳ ትንሽ ከፍ ስትል አስር አሰገዱ፡፡ በመቀጠል ፀሃይ ጠልቃ አድማሱ ከመጥፋቱ በፊት መግሪብ አሰገዱ፡፡ በመቀጠል የሌሊቱ ሲሶ (አንድ ሶሥተኛው) ካለፈ በኋላ ዒሻ አሰገዱ በመቀጠል ውጋገኑ ቢጫ ሲሆን ፈጅር አሰገዱ፡፡ በመቀጠል የአላህ መልዕክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ማነው ስለ ሰላት ወቅት የጠየቀኝ አሉ ? ጠያቂውም እኔ ነኝ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ አላቸው ፡፡ እሳቸውም (የሰላታችሁ ወቅት ባያቹሃቸው ጊዜያቶች መካከል ነው፡፡) አሏቸው

ሙስሊም እንደዘገበው

ይህ ከላይ የተዘረዘሩት የሰላት ወቅቶች የሚያመለክቱት በመጀመርው ቀን ያሰገዱት የሰላት ወቅቶች እንደገቡ ሲሆን በሁለተኛው ቀን ያሰገዱት የሰላት ወቅቶች መጨረሻ ላይ ነው በእርግጥ በሌላ ሐዲስ የኢሻ ሰላት እስከ እኩለ ሌሊት ማስረዘም ይቻላል ።

የሰላቶች የረከዓት ቁጥር ብዛት

1. የሱብሒ (ፈርድ) ሰላት ሁለት ረከዓት ሲሆን የሚቀራው ቁርአን ድምፅን በማውጣት (በጀሕርያ) ነው ፡ ከፊት ለፊቱ ሁለት ረከዓት ሱና አለው።
2. የዙሑር (ፈርድ) ሰላት የሚሰገደው አራት ረከዓት ሲሆን አራቱም ረከዓት ድምፅ ሳያወጡ (በሲር) ነው የሚቀራው ። ሱናው ከዙሁር ፈርድ ሰላት በፊት አራት ረከዓት ከዙሁር ፈርድ ሰላት በኋላ ሁለት ረከዓት ይሰገዳል።
3. የአሥር (ፈርድ) ሰላት የሚሰገደው አራት ረከዓት ሲሆን አራቱም ረከዓት ድምፅ ሳያወጡ (በሲሪያ) ነው የሚሰገደው።
4. የመግሪብ (ፈርድ) ሰላት የሚሰገደው ሦስት ረከዓት ሲሆን የመጀመርያዎቹ ሁለት ረከዓት ድምፅ አውጥቶ እየቀሩ (በጀሕርያ) ሲሰገድ የመጨረሻው አንድ ረከዓት ድምፅ ሳያወጡ (በሲሪያ) ነው የሚሰገደው።
5. የኢሻ ሰላት የሚሰገደው አራት ረከዓት ሲሆን የመጀመርያዎቹን ሁለት ረከዓት ድምፅ አውጥቶ እየቀሩ በጀሕርያ ሲሰገድ የመጨረሻዎቹን ሁለት ረከዓት ድምፅ ሳያወጡ (በሲሪያ) ነው የሚሰገደው።

የዊትር ሰላት ከኢሻ ሰላት በኋላ አንድ ፣ ሦስት ፣ አምስት ፣ ወይንም ሰባት ፣ ረከዓት ማለትም በጎዶሎ ቁጥር እያጠቃለሉ ይሰገዳል።

## በአናዳንድ ሰጋጆች ላይ በሰላት ጊዜ የሚታዩ ስህተቶች

1. ኒያ የሚደረገው (የሚታሰበው) በልብ ሲሆን ድምፅ አውጥቶ እንዲህ አይነት ሰላት ይህን ያህል ረከዓት ልሰግድ ነው ብሎ እየተናገሩ መነየት በሱና የማይታወቅ ነው። ኒያ ማለት በምላስ ሳይናገሩ በልብ ከአላህ ጋር የሚገናኙበት መንገድ ነው።
2. ለብቻ ሲሰገድ በመግቢያ ተክቢራ ላይ ድምፅን ሳያሰሙ ምላስን ሳያነቃንቁ ሳይሆን አላሁ አክበር ሲባል በመጠኑም ቢሆን ድምፅን በማሰማት ተገቢ ነው። መተጨማሪ በመጀመርያ ሁለት ረከዓት ላይ ከፋቲሐ በኋላ ምንም የቁርአን አንቀፅ ሳይቀሩ ሩኩዕ ማድረግ ስህተት ነው።

3. ሰላት ሲጀመር ሁለት እጆችን ወደ ጆሮ ግንድ ከፍ አድርጎ አላሁ አክበር እንደማለት ሆድ አካባቢ እጅን ብድግ አድርጎ አላሁ አክበር ማለት ስህተት ነው፡፡
4. ሰላት ሲቆም በቀኝ እጅ መዳፍ የግራ እጅ መዳፍ ወይንም ክንድን ጨበጥ አድርጎ መያዝ ሲሆን መዳፍን ዘርግቶ ልጥፍ ማድረግ ስህተት ነው፡፡ በተጨማሪ እጆች የሚያርፉት ደረት ላይ ነው እንጂ እንብርት ላይ ማሳረፍ ስህተት ነው፡፡
5. በሰላት ወቅት አይኖችን መጨፈን ፣ ንቅናቄ ማብዛት ፣ መቀለድ የመሳሰሉት ድርጊቶች ክልል ነው፡፡
6. ከሩኩዕ ሲነሱ (ረበና ለከል ሐምድ) ይባላል እንጂ (ረበና ለከል ሐምድ ወሹክር) ማለት ስህተት ነው ወሹክር የሚለውን ቃል መጨመር በሱና አይታወቅም፡፡
7. በተህያት ወቅት ሰላዋት ሲባል ሰይድና የሚለው ቃል በሰላት ውስጥ አይታወቅም፡፡

## በሰላት ላይ እያሉ ንግግር ስለመከልከሉ

**لحديث زيد بن أرقم: كنا نتكلم في الصلاة حتى نزلت فأمرنا بالسكوت ونهينا عن الكلام ، رواه الشيخان**

ዘይድ ቢን አርቀም (ረዲየላሁ ዓንሁ) በእንዳወሩት : (ወቁሙ ሊላሂ ቃኒቲን) የሚለው የቁርዓን አንቀፅ እስከሚወርድ ድረስ በሰላት ላይ እያለን እንነጋገር ነበር ሰውዬው አጠገቡ ያለውን ያናግረው ነበር በመጨረሻ

**{حَافِظُواْ عَلَى الصَّلَوَاتِ والصَّلاَةِ الْوُسْطَى وَقُومُواْ لِلّهِ قَانِتِينَ }البقرة238**

**ትርጉም ((በሶላቶች (በተለይ) በመካከለኛይቱም ሰላት ላይ ተጠባበቁ ታዛዦች ሆናችሁም ለአላህ ቁሙ ))** *አል በቀራህ 238*
*የሚለው የቁርአን አንቀፅ ሲመጣ በሰላት ላይ ፀጥ እንድንል ታዘዝን መነጋገርም ተከለከልን አሉ፡፡* ቡኻሪና ሙስሊምእንደዘገቡት፡፡

# ወደ ቀብር ዞሮ መስገድ ስለመከልከሉ

አቢ መርሰድ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳሉት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ቀብር ላይ እንዳትቀመጡ ወደቀብርም ዞራችሁ እንዳትሰግዱ) ብለዋል፡፡ *ሙስሊም እንደዘገቡት 972*

ለትክክለኛ ሰላት መሟላት ቅድመ ሁኔታዎች

1. የአዕምሮ ባለቤት
2. ሙስሊም የሆነ
3. ጧሃራ ማድረግ
4. የሰላት ወቅት መግባት ናቸው

ሰላት ግዴታ የሚሆንባቸው

1. የአዕምሮ ባለቤት
2. ሙስሊም የሆነ
3. ለአካለ መጠን የደረሰ

## ሰላት የሚያበላሹ ክስተቶች

1. ጧሃራ ሲፈርስ ይኸውም (በውሃም ሆነ በደረቅ ሽንት እና ንፋስ ከሆድ በመውጣቱ ሰበብ ውዱእ ይፈርሳል ::
2. ሰላት ውስጥ እያሉ መብላት መጠጣትና ለሰላት አስፈላጊ ያልሆነ ንግግር መናገር ሰላት ያበላሻል::
3. አውረት ያለመሸፈን ሰላት ያበላሻል
4. በሰላት ወቅት የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ማብዛት
5. እያወቁ የቂብላን አቅጣጫ መሳት:: የመሳሰሉት በጠቅላላ ሰላት ያበላሻሉ::

## ተውሒድ
## አሥር ከኢስላም የሚያወጡ ወንጀሎች

**1ኛ -** ለአላህ የሚገባውን የዒባዳ አይነቶችን አሳልፎ ለፍጡር መስጠት ትልቅ ሽርክ ነው ::ይኸውም
ሀ - ከመላይኮች ከነብያቶችና ከሷሊህ ሰዎች እርዳታ መከጀል
ለ - ከሞተ ሰው እርዳታ መጠየቅ ፤፤
ሐ- ለፍጡር መሳል ፤ መስገድና ፤ የፈጣሪን ሥራ አሳልፎ ለፍጡር መስጠት ሁሉ ትልልቅ ሽርኮች ናቸው ::
አላህ ለሙስሊሞች የፈለገውን ወንጀላቸውን ሊምር ቃል ገብቶዋል ማሻረክን ግን ፈፅሞ እንደማይምር በሚቀጥለው የቁርአን አንቀፅ ገልፆታል ::

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ۚ وَمَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا ﴿١١٦﴾ ﴾ النساء: ١١٦

**ትርጉሙም (( አላህ በሱ የሚያሻርክን አይምርም ( ከሽርክ ) ሌላ የሆነውን ( ወንጀል ) ለፈለገ ይምራል በአላህ የሚያሻርክ ሰው (ከእውነት ) የራቀን መሳሳት በርግጥ ተሳሳተ ))** ኒሳእ-116

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ إِنَّهُۥ مَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِ ٱلْجَنَّةَ وَمَأْوَىٰهُ ٱلنَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾ ﴾ المائدة: ٧٢

***ትርጉሙም (( እነሆ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በዕርግጥ እርም አደረገ መኖርያውም እሳት ናት ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም ))*** አል - ማኢዳህ - 72

በእርግጥ ባለማወቅም ሆን በድፍረት ብዙዎች በኢስላም ስም እየተጠሩ ሥራቸው ከኢስላም ውጪ የሆኑ አሉ ስለዚህ እያወቁ በአላህ የሚያሻርኩ ሃያሉን አላህ ሊፈሩት ይገባል :: ባለማወቅ በአላህ የሚያሻርኩ በሽርክ ምንም ምክንያት ማቅረብ የማይቻልበትን ቀን የውመል ቂያማ በማስታወስ ዲናቸውን ጠንቅቀው ማወቅና አላህን መፍራት ይገባቸዋል ::

**2ኛ -** በራሱና በአላህ መካከል አማላጅ የሚያስገባ ፈጣሪን በመተው ከፍጡር እርዳታ መጠየቅና ከአላህ ጋር ያቃርበኛል ብሎ በሕይወትም ያለን ሆነ በሞት የተለየን ፍጡር ለመንፈሳዊ እርዳት መጥራት ከኢስላም የሚያወጣ ትልቅ ወንጀል ነው ::
በዚህ ጉዳይ ላይ አላህ በቁርአኑ ሲያስጠነቅቅ እንዲህ ይላል :

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَأَنَّ ٱلْمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا۟ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدًا ﴿١٨﴾ ﴾ الجن: ١٨

**ትርጉሙም ((እነሆ መስጊዶች የአላህ ብቻ ናቸው (በውስጣቸውም) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ ))** ሱረቱል ጂን - 18

**3ኛ-** ከኢስላም ውጪ ያሉ ሐይማኖቶች ትክክል ይሆናሉ ብሎ መገመት ወይንም ትንሽም ቢሆን መጠራጠር በኢስላም ትልቅ ወንጀል በመሆኑ ያከፍራል ::
አላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ለመሆኑ በሚቀጥለው የቁርአን አንቀፅ አላህ እንደሚከተለው ገልፆታል ::

قَالَ تَعَالَىٰ: أَعُوذُ بِٱللَّهِ مِنَ ٱلشَّيْطَٰنِ ٱلرَّجِيمِ ﴿ وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ ٱلْإِسْلَٰمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٨٥﴾ ﴾ آل عمران: ٨٥

**ትርጉሙም (( ከእስልምና በስተቀር « ሌላ» ሃይማኖት የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም በመጪው ዓለምም ከከሳሪዎቹ ነው ))** *ዒምራን ኘ 85*

**4ኛ -** አንድ ሙስሊም አላህ እና መልዕክተኛው ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) ከደነገጉት የሸሪዓ ሕግ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚቃረንና ሰው ሰራሽ ጣዖታዊ ሕግ ይሻላል ካለ የኩፍር ቃል ተናገረ ማለት ነው ::

## ለምሳሌ

**ሀ -** ከኢስላም ሸሪዓ ሰዎች ያፀደቁት ደንብና ሕግ ይሻላል ማለት::
**ለ -** ያለንበት ዘመን ከኢስላም ሸሪዐ ጋር አይገጥምም ብሎ የአላህ ሸሪዓን ማጣጣል ::
**ሐ -** ለሙስሊሞች ኋላቀርነትና ድህነት ሰበቡ ኢስላም ነው ብሎ ደካማ ምክንያት ማቅረብ :
**መ -** የሰረቀን እጁን መቁረጥ የባለትዳር ዝሙተኞችን መግደል ያላገቡ ዝሙተኞችን መቶ መግረፍ የመሳሰሉትን የሸሪዓ ሕጎች ለዚህ ዘመን አይሆንም ጭካኔ ነው ብሎ በፈጣሪ ሥራ ገብቶ መቀባጠር :
**ሠ -** በቁርአንና በሐዲስ ሐራምነታቸው የተረጋገጠ እንደ አስካሪ መጠጥ መጠጣትና ማጠጣት፣ ወይንም መሸጥ፣ አራጣ መብላትና ማብላት፣ ከሸሪዐ ውጪ መፍረድና ማስፈረድ የመሳሰሉትን ለችግር ከሆነ ምንም አይደለም ብሎ የፈጣሪን ሕግ ለማሻሻል መዳፈር ባጠቃላይ ካለይ የተዘረዘሩትን ወንጀሎች መደገፍና መተግበር ከኢስላም የሚያወጡ ወንጀሎች ናቸው ::

**5ኛ -** በሸሪዓ የተደነገጉ ሕጎችን በጥላቻ መቀበል ከወንጀልነትም አልፎ ሥራን ያበላሻል በአላህና በረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የታዘዝናቸው ትዕዛዞች ሁሉ በደስታ መቀበልና መፈፀም የሙስሊም ግዴታ ነው አላህም በቁርአኑ::

قَالَ تَعَالَىٰ: أَعُوذُ بِٱللَّهِ مِنَ ٱلشَّيْطَٰنِ ٱلرَّجِيمِ ﴿ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ فَتَعْسًا لَّهُمْ وَأَضَلَّ أَعْمَٰلَهُمْ ﴿٨﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ كَرِهُوا۟ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ فَأَحْبَطَ أَعْمَٰلَهُمْ ﴿٩﴾ ﴾ محمد: ٨ - ٩

**ትርጉሙም ((እነዚያም የካዱት ለነሱ ጥፋት ተገባቸው ሥራዎቻቸውንም አጠፋንባቸው «» ይህ እነሱ አላህ ያወረደውን ስለጠሉ ነው ስለዚህ ሥራዎቻቸውን አበላሸንባቸው ))** *መሐመድ*-**8-9**

**6ኛ** - *ድግምት መሥራት ይኸውም ሰዎች የሚወዱትን ነገር በድግምት እንዲጠሉት ማድረግ ወይንም የሚጠሉትን ነገር እንዲወዱት ማድረግ ፣ መተናኮልና ፣ ሰይጣናዊ መስተፋቅር መስራት የመሳሰሉት ሁሉ እስካልቶበቱ ድረስ የሚያከፍሩ ወንጀሎች ናቸው ከቁርዓን መረጃ:-*

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَٱتَّبَعُواْ مَا تَتۡلُواْ ٱلشَّيَٰطِينُ عَلَىٰ مُلۡكِ سُلَيۡمَٰنَۖ وَمَا كَفَرَ سُلَيۡمَٰنُ وَلَٰكِنَّ ٱلشَّيَٰطِينَ كَفَرُواْ يُعَلِّمُونَ ٱلنَّاسَ ٱلسِّحۡرَ ﴾ البقرة: ١٠٢

**ትርጉሙም (( ሰይጣናትም በሱለይማን ዘመነ መንግስት የሚያነቡትን « ድግምት » ተከተሉ ሱለይማንም አልካደም ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምት የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ ))**

**አል በቀራህ - 102**

**7ኛ** - በአላህ በረሱል በቁርአንና በሐዲስ ባጠቃላይ በዲን መቀለድ የውሸትም ቢሆን እንደሚያከፍር አላህ በቁርአኑ ሲያስጠነቅቅ እንዲህ ይላል ፡-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَلَئِن سَأَلۡتَهُمۡ لَيَقُولُنَّ إِنَّمَا كُنَّا نَخُوضُ وَنَلۡعَبُۚ قُلۡ أَبِٱللَّهِ وَءَايَٰتِهِۦ وَرَسُولِهِۦ كُنتُمۡ تَسۡتَهۡزِءُونَ ٦٥ لَا تَعۡتَذِرُواْ قَدۡ كَفَرۡتُم بَعۡدَ إِيمَٰنِكُمۡۚ ﴾ التوبة: ٦٥ ـ ٦٦

**ትርጉሙም (( በእርግጥ ብትጠይቃቸው እኛ የምንዘባርቅና የምንጫወት ብቻ ነበርን ይላሉ በአላህ እና በአንቀጾቹ በመልዕክተኛ ውም ታላግጡ ነበራችሁን ? በላቸው «» አታማካኙ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ .... ))** ተውባ **65 - 66**

**8ኛ** - *ከሙሽሪኮችና ከካፊር ተመሳጥሮ ሙስሊምን ማጥቃት ከእስልምና ማፈንገጥ (ኒፋቅ) ነው ::*

**9ኛ** -*ሙስሊም ነኝ እያሉ ሕይወትን ከሸሪዓ ውጪ መምራትና ሌላ ሥርዓት መምረጥ ያከፍራል ::*

**10ኛ** - *በግልፅ ኢስላምን መቃወም ወይንም የኢስላም እምነት መሠረት የሆኑትን መመሪያዎች ሳይማሩና ሳይጠይቁ በቸልተኝነት*

ተዘናግቶ ለኩፍርና ለሽርክ ሥራዎች መዳረግ በእምነት ላይ አደጋ ያስከትላል አላህ በቁርዓኑ ሲያስጠነቅቅ :-

قَالَ تَعَالَىٰ: ﴿ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن ذُكِّرَ بِـَٔايَـٰتِ رَبِّهِۦ ثُمَّ أَعْرَضَ عَنْهَآ ۚ إِنَّا مِنَ ٱلْمُجْرِمِينَ مُنتَقِمُونَ ﴿٢٢﴾ ﴾ السجدة: ٢٢

**ትርጉሙ (( በጌታው አንቀፆች ከተገሠፀና ከዚያም ከተወው ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? እኛ ከተንኮለኞቹ እንበቀላቸዋለን)** ሰጅዳህ ኘ 22

ከላይ የተዘረዘሩትን የኢማን ጠንቆች ሁሉ የተገደደ ሲቀር በቀልድም ሆነ በምር ወይንም ሰውን ፍራቻ የፈፀመ ሳያውቀው ከኢስላም የሚያወጣው ወንጀል ፈፀመ ማለት ነው ስለዚህ እንደቀልድ የምናያቸውና የምንንቃቸው ወንጀሎች ከኢስላም ስለሚያወጡ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ::

በራሂን በሚል ስያሜ የተዘጋጀው ስለኢስላምና ኢማን መሠረቶች የሚብራራ ፁሁፍ በዚሁ ይጠቃለላል ::

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه وسلم .